# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## ምዕራፍ ፩

### ስለ መጠራቱ

፩የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማስተማር ተለ
ይቶ ከተጠራ ሐዋርያ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክር
ስቶስ አገልጋይ ከሚሆን ከጳውሎስ፥ ፪በነቢያቱ
ቃልና በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ በተስፋ
ያናገረው፥ ፫ከዳዊት ዘር ሰው ሆኖ በሥጋ ስለ
ተወለደ ስለ ልጁ፥ ፬የእግዚአብሔር ልጅ እንደ
ሆነ በኀይሉና በመንፈስ ቅዱስ፥ ከሙታንም
ተለይቶ በመነሣቱ ስለ አሳየ ስለ ጌታችን ኢየ
ሱስ ክርስቶስ፥ ፭በስሙ እንዲያምኑ አሕዛብን
ልናስተምር ሐዋርያት ተብለን የተሾምንበትና
ጸጋን ያገኘንበት፥ ፮እናንተም ዛሬ በኢየሱስ
ክርስቶስ ለማመን እንደ ተጠራችሁ። ፯በሮሜ
ላላችሁ፥ እግዚአብሔር ለሚወዳችሁ፥ ለመረ
ጣችሁና ላከበራችሁ ሁሉ፥ ከአባታችን ከእግዚ
አብሔር፥ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስም ሰላ
ምና ጸጋ ለእናንተ ይሁን።

፰አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ በኢየሱስ ክርስ
ቶስ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፤ ማመና
ችሁ በዓለም ሁሉ ተሰምታለችና። ፱ባለማቋረጥ
በምጸልየው ጸሎት እንደማስባችሁ ልጁ በአስ
ተማረው ወንጌል በፍጹም ልቡናዬ የማመል
ከው እግዚአብሔር ምስክሬ ነው። ፲ወደ እና
ንተ እመጣ ዘንድም እግዚአብሔር በፈቃዱ
መንገዴን ያቃናልኝ ዘንድ ዘወትር እጸልያለሁ።
፲፩ትጸኑ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንድ
ታገኙ ላያችሁ እወዳለሁና፤ ፲፪ይህንም ማለቴ
በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት
አብረን በእናንተ እንድንጽናና ነው። ፲፫ነገር ግን
ወንድሞቻችን ሆይ፥ በሌሎች አሕዛብ እንደ
ሆነ በእናንተም ዋጋዬን አገኝ ዘንድ ሁልጊዜ
ወደ እናንተ ልመጣ እንደ ወደድሁ፥ እስከ ዛሬ
ድረስም እንደ ተሳነኝ ልታውቁ እወድዳለሁ።
፲፬ለአረማውያንና ላልተማሩ፥ ለጥበበኞችና ለማ
ያስተውሉም ሁሉ አስተምር ዘንድ ዕዳ አለ
ብኝ። ፲፭ይልቁንም በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ
ወንጌልን ላስተምራችሁ እተጋለሁ።

፲፮ወንጌልን ለማስተማር አላፍርምና፤ አስቀ
ድሞ አይሁዳዊን፥ ደግሞም አረማዊን፥ የሚያ
ምኑበትን ሁሉ የሚያድናቸው የእግዚአብሔር
ኀይሉ ነውና። ፲፯"ጻድቅ በእምነት ይኖራል"
ብሎ መጽሐፍ እንደ ተናገረ የእግዚአብሔር
ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለ
ጣልና።

### በኃጥአን ላይ ስለሚመጣው መቅሠፍት

፲፰እውነትን ዐውቀው በክፋታቸው በሚሰው
ሩአት በዐመፀኛውና በኀጢአተኛው ሰው ሁሉ
ላይ የእግዚአብሔር መቅሠፍት ከሰማይ ይመ
ጣል። ፲፱እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው እግዚ
አብሔርን ማወቅ በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና።
፳የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ እርሱም
የዘለዓለም ኀይሉና ጌትነቱ ከዓለም ፍጥረት
ጀምሮ የፈጠረውን ፍጥረት በማሰብና በመመ
ርመር ይታወቃል፤ መልስ የሚሰጡበትን ምክ
ንያት እንዳያገኙ። ፳፩እግዚአብሔርን ሲያው
ቁት እንደ እግዚአብሔርነቱ አላከበሩትም፤
አላመሰገኑትምም፤ ነገር ግን ካዱት፤ በአሳባቸ
ውም ረከሱ፤ ልቡናቸውም ባለማወቅ ጨለመ።
፳፪ጥበበኞች ነን ሲሉ አላዋቆች ሆኑ። ፳፫የማይሞ
ተውን የእግዚአብሔርን ክብር በሚሞት ሰውና

---

፩፥፩ ሐ.ሥ. ፱፥፲፭። ፩፥፫ ማቴ. ፩፥፮-፲፮። ፩፥፬ ሐ.ሥ. ፲፫፥፴፫። ፩፥፭ ገላ. ፩፥፲፭፡፲፮።
፩፥፱ ፪ጢሞ. ፩፥፫። ፩፥፲፫ ሐ.ሥ. ፲፱፥፳፩። ፩፥፲፮ ማር. ፰፥፴፰። ፩፥፲፯ ዕን. ፪፥፬።
፩፥፳፩ ኤፌ. ፬፥፲፯-፲፰። ፩፥፳፫ ዘዳ. ፬፥፲፮-፲፰።

ወፎች፥ አራት እግር ባላቸውም፥ በሚንቀሳቀ
ሱትም መልክ መሰለው ለወጡ።
፳፬ስለዚህም እግዚአብሔር እርስ በርሳቸው
ሥጋቸውን ሊያዋርዱ በልባቸው ፍትወት ወደ
ርኵሰት አሳልፎ ተዋቸው። ፳፭የእግዚአብሔ
ርን እውነት ሐሰት አድርገዋታልና፤ ተዋርደ
ውም ፍጥረቱን አምልከዋልና፤ ሁሉን የፈጠረ
ውን ግን ተዉት፤ እርሱም ለዘለዓለም ቡሩክ
አምላክ ነው፤ አሜን።
፳፮ስለዚህም እግዚአብሔር ከፉ መቅሠፍትን
አመጣባቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚ
ገባቸውን ትተው ለባሕርያቸው የማይገባውን
ሠሩ። ፳፯ወንዶችም እንዲሁ ለባሕርያቸው የሚ
ገባውን ሴቶችን ትተው በፍትወት ተቃጠሉ፤
እርስ በርሳቸውም እየተመላለሱ፥ ወንዶች በወ
ንዶች ላይ የሚያዋርዳቸውን ነውር ሠሩ፤ ነገር
ግን ፍዳቸውን ያገናሉ፤ ፍዳቸውም በራሳቸው
ይመለሳል። ፳፰እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወ
ደዱ መጠን እንዲሁ እግዚአብሔር ይህን የማይ
ገባውን ይሠሩ ዘንድ ሰነፍ አእምሮን ሰጣቸው።
፳፱እነርሱም ዐመፅን ሁሉ፥ ክፋትንም፥ ምኞት
ንም፥ ቅሚያንም፥ ቅናትንም የተመሉ ናቸው፤
ምቀኞች፥ ነፍስ ገዳዮች፥ ከዳተኞች፥ ተንኰለ
ኞች፥ ኩሩዎች፥ ጠባያቸውንና ግብራቸውንም
ያከፉ ናቸው። ፴ሐሜተኞች፥ እግዚአብሔርን
የሚጠሉ፥ ተሳዳቢዎች፥ ትዕቢተኞች፥ ትም
ክሕተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ ለወላጆቻቸ
ውም የማይታዘዙ ናቸው። ፴፩የማያስተውሉ፥
ዝንጉዎች፥ ፍቅርም፥ ምሕረትም የሌላቸው
ናቸው። ፴፪ይህን እንዲህ ላደረገ ሞት እንደሚገ
ባው እነርሱ ራሳቸው የእግዚአብሔርን ፍርድ
እያወቁ፥ እነርሱ ብቻ የሚያደርጉት አይደለም፤
ነገር ግን ሌላውን ያነሣሡታል፤ ያሠሩታልም።

## ምዕራፍ ፪

### ወንድሙን ስለሚነቅፍ ሰው

፩አንተ ሰው ሆይ፥ እውነት ለሚፈርደው ለእ
ግዚአብሔር ምን ትመልስለታለህ?[፩] በወንድምህ
ላይ የምትጠላውን ያን ሥራ አንተ ራስህ ከሠ
ራኸው በራስህ የምትፈርድ አይደለምን? አንተ
ራስህ ያን ሥራ ትሠራዋለህና። ፪ይህም እንደዚህ
በሚያደርጉ ሰዎች ላይ ቅጣት የሚያመጣ[፪] የእ
ግዚአብሔር ፍርዱ እውነት እንደ ሆነ እናውቃ
ለን። ፫አንተ ሰው ሆይ፥ በሌላ ላይ አይተህ የም
ትጠላውንና የምትነቅፈውን ያን አንተ ራስህ
የምትሠራው ከሆነ፥ ከእግዚአብሔር ፍርድ
እንደምታመልጥ ታስባለህን? ፬ወይስ በቸርነቱ
ብዛት በመታገሡ፥ ለአንተም እሺ በማለቱ እግ
ዚአብሔርን አላዋቂ ልታደርገው ታስባለህን?
የእግዚአብሔርስ ቸርነቱ አንተን ወደ ንስሓ እን
ዲመልስህ አታውቅምን? ፭ነገር ግን ልቡናህን
እንደ ማጽናትህ፥ ንስሓም እንደ አለመግባትህ
መጠን የእግዚአብሔር እውነተኛ ፍርድ በሚገ
ለጥበት ቀን መቅሠፍትን ለራስህ ታከማቻለህ።
፮እርሱ በእውነተኛ ፍርዱ[፫] ለሁሉ እንደ ሥራው
ይከፍለዋልና። ፯በበጎ ምግባር ጸንተው ለሚታ
ገሡ፥ ምስጋናና ክብርን፥ የማይጠፋ ሕይወት
ንም ለሚሹ እርሱ የዘለዓለም ሕይወትን ይሰ
ጣቸዋል። ፰ለሚክዱና እውነትን ለሚለውጡ፥
ዐመፅንም ለሚወድዱ ሰዎች ዋጋቸው ቍጣና
መቅሠፍት ነው። ፱መከራና ጭንቀት አስቀድሞ
በአይሁዳዊ፥ ደግሞም በአረማዊ፥ ሥራዉ ክፉ
በሆነ ሰው ሁሉ ላይ ነው። ፲ምስጋናና ክብር፥
ሰላምም አስቀድሞ ለአይሁዳዊ፥ ደግሞም ለአረ
ማዊ፥ ሥራዉ መልካም ለሆነ ሁሉ ነው። ፲፩እግ
ዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና።
፲፪ከሕግ ወጥተው የበደሉ በሕግ ይፈረድባቸ
ዋል፤ ያለ ሕግ የበደሉ ሁሉም ያለ ሕግ ይፈረ
ድባቸዋል። ፲፫በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚ
ያደርጉ ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ አይ
ጸድቁምና። ፲፬ሕግ የሌላቸው አሕዛብስ እንኳ
ለራሳቸው ሕግ ይሠራሉ፤ ራሳቸው ለራሳቸው
ሕግን ይደነግጋሉ፤ በሕጋቸው የታዘዘውንም
ያደርጋሉ።[፬] ፲፭በልባቸው የተጻፈውን የሕግ
ሥራ ያሳያሉ፤ ከሥራቸውም የተነሣ ይታወ
ቃል፤ ሕሊናቸውም ይመሰክርባቸዋል፤ ይፈር
ድባቸዋልም። ፲፮ይህም እግዚአብሔር በኢየሱስ

---

፩ "እውነት ለሚፈርደው ለእግዚአብሔር ምን ትመልስለታለህ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ "... ቅጣትን የሚያመጣ ..." የሚለው በግእዝ ብቻ።

፫ "... በእውነተኛ ፍርዱ" የሚለው በግእዝ ብቻ።

፬ ግሪኩ "ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ያደርጋሉ፤ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸውም እንኳ ለራሳ
ቸው ሕግ ናቸውና" ይላል።

፩፥፳፪ ሆሴዕ ፯፥፩-፫።     ፪፥፩ ማቴ. ፯፥፩፤ ሉቃ. ፮፥፴፯።     ፪፥፮ መዝ. ፷፪፥፲፪፤ ምሳ. ፳፬፥፲፪።
፪፥፲፩ ዘዳ. ፲፥፲፯።

ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳስተማርሁ ስዎችን በልቡናቸው የሰወሩትንና የሸሸጉትን በሚመረ ምርበት ጊዜ የሚናገሩትና የሚመልሱት እንደ ሌለ ስለሚያውቁ ነው።

### ራሱ የማይሠራ ለሌላው የሚያስተምር

፲፯አንተ አይሁዳዊ፥ በኦሪትህ የምታርፍ፥ በእ ግዚአብሔርም የምትመካ ከሆንህ፥ ፲፰ፈቃዱን የምታውቅ፥ መልካሙንም የምትለይ፥ ኦሪ ትንም የተማርህ ከሆንህ፥ ፲፱አንተ የዕውሮች መሪ፥ በጨለማም ላሉት ብርሃን እንደ ሆንህ በራስህ የምትታመን ከሆንህ፥ ፳ሰነፎችን ልባ ሞች የምታደርግ፥ ሕፃናትን የምታስተምር፥ ጻድቅና የምትከብርበትን የኦሪትን ሕግ የምታ ውቅ የምትመስል፥ ፳፩እንግዲህ ሌላውን የምታ ስተምር ራስህን እንዴት አታስተምርም? አት ስረቁ ትላለህ፤ ነገር ግን አንተ ራስህ ትሰርቃ ለህ። ፳፪አታመንዝሩ ትላለህ፤ ነገር ግን አንተ ራስህ ታመነዝራለህ፤ ወደ ጐልማሳ ሚስትም ትሄዳለህ፤[፫] ጣዖትን ትጸየፋለህ፤ አንተ ግን ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህ። ፳፫በኦሪት ትመካ ለህ፤ ነገር ግን አንተ ራስህ ኦሪትን በመሻር እግዚአብሔርን ታቃልለዋለህ። ፳፬እንደ ተጻፈም “እነሆ፥ በእናንተ ምክንያት አሕዛብ የእግዚአ ብሔርን ስም ይሰድባሉ።”

### ስለ ግዝረትና ስለ አይሁዳዊነት

፳፭ኦሪትንም ብትፈጽም ግዝረት ትጠቅምሃ ለች፤ ኦሪትን ባትፈጽም ግን ግዝረትህ አለመገ ዘር ትሆንብሃለች። ፳፮አንተ ሳትገዘር ብትኖር፥ ኦሪትንም ብትጠብቅ አለመገዘርህ መገዘር ትሆ ንልሃለች። ፳፯ተገዝረህ ኦሪትን ከምታፈርስ በተ ፈጥሮ ያገኘሃት አለመገዘርህ አብራህ ብትኖር ይሻልሃል፤[፬] ኦሪትን ከምታፈርስ ከአንተ ከተገዘ ርኸው ያ ያልተገዘረው፥ ኦሪትን የሚፈጽመው ይሻላል። ፳፰በውኑ ለሰው ይምሰል አይሁዳዊ መሆን ይገባልን? ለሰው ፊትስ ተብሎ ይገዘሩ አልን? ፳፱ዳሩ ግን አይሁዳዊነት በስውር ነው፤ መገዘርም በመንፈስ የልብ መገዘር እንጂ በኦ ሪት ሥርዐት አይደለም፤ ምስጋናውም ከእግዚ አብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም።

## ምዕራፍ ፫

### ስለ አይሁዳዊነት ጥያቄ

፩እንግዲህ አይሁዳዊ የመባል ትርፉ ምን ድን ነው? የግዝረትስ ጥቅምዋ ምንድን ነው? ፪በሁሉ ነገር ብዙ ነው፤ ነገር ግን ከዚያ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃል አደራ ተሰጣ ቸው። ፫የማያምኑ ቢኖሩስ የእነርሱ አለማመን ሌላውን በእግዚአብሔር እንዳያምን ይከለክላ ልን? አይከለክልም። ፬መጽሐፍ፥ “በነገርህ ትጸድቅ ዘንድ፥ በፍርድህም ታሸንፍ ዘንድ” ብሎ እንደ ተናገረ እግዚአብሔር እውነተኛ ነውና፥ ሰውም ሁሉ ሐሰተኛ ነውና። ፭በእኔ ኀጢአት[፭] የእግዚአብሔር ጽድቅ ከጸና እን ግዲህ ምን እንላለን? እግዚአብሔር በሰው ላይ ቅጣትን ቢያመጣ ይበድላልን? አይበድ ልም፤ የምናገረውንም በሰው ልማድ እናገራ ለሁ። ፮እንዲህማ ከሆነ እግዚአብሔር በዓለም እንደምን ይፈርዳል? ፯የእግዚአብሔር እው ነት በእኔ ሐስተኛነት ለክብሩ ከፍ ከአለ እን ግዲህ እኔን እንደ ኀጢአተኛ ለምን ይፈርድ ብኛል? ፰በውኑ እኛ መልካም ነገር እናገኝ ዘንድ ክፉ ነገር እናድርግ እንደምንል አስመ ሰለው የሚጠረጥሩንና የሚነቅፉን ሰዎች እን ደሚሰድቡን ነን? ለእነርሱስ ቅጣታቸው ተዘ ጋጅቶላቸዋል።

፱እንግዲህ ምን እንላለን? ከእነርሱ እንበ ልጣለን? አይደለም፤ አይሁዳዊንም፥ አረ ማዊንም እነሆ፥ አስቀድመን ነቅፈናቸዋል፤ ሁሉም ስተዋልና። ፲መጽሐፍ እንዲህ እንዳለ “አንድ ስንኳ ጻድቅ የለም። ፲፩አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚሻው የለም። ፲፪ሁሉም ተባብሮ በደለ፤ በጎ ሥራንም የሚ ሠራ የለም፤ አንድ ስንኳ ቢሆን የለም። ፲፫ጉሮ ሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው፤ በአንደ በታቸውም ሸንገሉ፤ ከከንፈሮቻቸውም በታች የእባብ መርዝ አለ፤ ፲፬አፉቸው መራራ ነው፤ መርገምንም የተሞላ ነው። ፲፭እግሮቻቸውም ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው። ፲፮በመንገ ዳቸው ጥፋትና ጕስቍልና አለ። ፲፯የሰላምን

---

፫ “ወደ ጐልማሳ ሚስትም ትሄዳለህ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ “በተፈጥሮ ያገኘሃት አለመገዘርህ አብራህ ብትኖር ይሻላል” የሚለው በግሪኩ የለም።

፭ ግሪኩ “በእኛ ኀጢአት ...” ይላል።

፪፥፳፬ ኢሳ. ፶፪፥፭። ፪፥፳፱ ዘዳ. ፴፥፮። ፫፥፬ መዝ. ፶፥፬። ፫፥፲-፲፪ መዝ. ፲፫፥፩-፫፤ ፶፪፥፩-፫። ፫፥፲፫ መዝ. ፭፥፱፤ ፻፴፱፥፫። ፫፥፲፬ መዝ. ፲፥፯። ፫፥፲፭-፲፯ ኢሳ. ፶፱፥፯-፰።

መንገድ አያውቋትም። ፲፰በዐይኖቻቸውም
ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም።"
፲፱እንደበት ሁሉ ይዘጋ ዘንድ፥ ዓለምም ሁሉ
ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ
አሪት የሚናገረው ሁሉ በአሪት ላሉት እንደ
ተነገረ እናውቃለን። ፳ከአሪት የተነሣ ኀጢአት
ስለ ታወቀች ሰው ሁሉ የአሪትን ሥርዐት በመ
ፈጸም በእግዚአብሔር ፊት አይጸድቅም።
፳፩አሁን ግን በአሪትና በነቢያት የተመሰከ
ረላት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ አሪት ተገለ
ጠች። ፳፪የሚያምኑበት ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶ
ስን በማመን በእግዚአብሔር ዘንድ ይጸድቃሉ።
፳፫በዚህም ልዩነት የለም፤ ሁሉም ፈጽመው
በድለዋልና፤ እግዚአብሔርን ማክበርንም ትተ
ዋልና። ፳፬ጽድቅ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት
ያለ ዋጋ በአርሱ ቸርነት ሆነ። ፳፭እርሱንም እግ
ዚአብሔር በእምነት የሚገኝ፥ በደሙም የሆነ
ማስተስረያ አድርጎ አቀመው፤ ይህም ከጥንት
ጀምሮ በበደሉት ላይ ጽድቁን ይገልጥ ዘንድ
ነው። ፳፮እግዚአብሔር ታጋሽ በመሆኑ፥ እሺ
በማለቱም እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ፥ በኢየሱስ
ክርስቶስም የሚያምኑትን እንደሚያጸድቃቸው
ዛሬ ያውቁ ዘንድ ነው። ፳፯ትምክሕት ወዴት
አለ? አርሱ ቀርቶአል፤ በየትኛውስ ሕግ ነው?
በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፤ በእምነት ሕግ
ነው እንጂ። ፳፰ሰው የአሪትን ሥራ ሳይሠራ በእ
ምነት እንዲጸድቅ እናውቃለንና። ፳፱በውኑ እግ
ዚአብሔር ለአይሁድ ለብቻቸው ነውን? ለአሕ
ዛብስ አይደለምን? ፴አዎን፥ ለአሕዛብም ነው፤
የተገዘረውን በእምነት የሚያጸድቅ፥ ያልተገዘ
ረውንም በእምነት የሚያጸድቀው እርሱ አንዱ
እግዚአብሔር ነውና። ፴፩እንግዲህ በእምነት አሪ
ትን እንሽራለን? አንሽርም፤ አሪትን እናጸና
ለን እንጂ።

## ምዕራፍ ፬

### የአብርሃም ምሳሌነት

፩እንግዲህ በሥጋ የቀድሞ አባታችን የሆነው
አብርሃም ምን አገኘ እንላለን? ይህን በሥራው
አግኝቶአልን? ፪አብርሃም በሥራው ጸድቆስ
ቢሆን ትምክሕት በሆነው ነበር፤ ነገር ግን
በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም። ፫መጽሐፍስ
ምን ይላል? አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤
ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት። ፬ለሚሠራ ዋጋው
እንደሚገባው እንጂ በለጋስነት እንደ ስጦታ
ሆኖ አይቈጠርበትም። ፭ለማይሠራ ግን ኀጢአ
ተኛውን በሚያጸድቀው ካመነ እምነቱ ጽድቅ
ሆኖ ይቈጠርለታል። ፮የአሪትን ሥራ ሳይፈጽም
ማመኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ጽድቅ ሆኖ የሚ
ቈጠርለትን ሰው ዳዊት "ብፁዕ" በሚልበት
አንቀጽ እንዲህ ይላል፦ ፯"መተላለፋቸው የቀ
ረላቸው፥ ኀጢአታቸውም የተሰረየላቸው ብፁ
ዓን ናቸው። ፰እግዚአብሔርም በደሉን የማይ
ቈጥርበት ሰው ብፁዕ ነው።"
፱እንግዲህ ይህ ብፅዕና ስለ መገዘር ተነገረን?
ወይስ ስለ አለመገዘር? እምነቱ ለአብርሃም
ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት እንላለንና። ፲ለአብ
ርሃም ጽድቅ ሆኖ የተቈጠረለት መቼ ነው?
ተገዝሮ ሳለ ነውን? ወይስ ሳይገዘር? ሳይገዘር
ነው እንጂ ተገዝሮ ሳለ አይደለም። ፲፩ሳይገዘር
እግዚአብሔር አብርሃምን በእምነት እንደ አጸ
ደቀው በእርሱ ላይ ይታወቅ ዘንድ ግዝረትን
የጽድቅ ማኅተም ትሆነው ዘንድ ምልክት አድ
ርጎ ሰጠው። ሳይገዘሩ ለሚያምኑ ሁሉ አባት
ሊሆን፥ አብርሃም በእምነት እንደ ከበረ እነ
ርሱም በእምነት እንደሚከብሩ ያውቁ ዘንድ
ሰጠው። ፲፪ለተገዘሩትም አባት ይሆን ዘንድ
ነው፤ ነገር ግን ለተገዘሩት ብቻ አይደለም፤
እርሱ አባታችን አብርሃም ሳይገዘር እንደ አመነ
ሳይገዘሩ የአባታችን የአብርሃምን የሃይማኖቱን
ፍለጋ ለሚከተሉ ደግሞ ነው እንጂ።

### ስለ አብርሃምና ስለ ዘሩ ተስፋ

፲፫አብርሃም፥ ዘሩም ዓለምን ይወርስ ዘንድ
ተስፋ ያገኘ የአሪትን ሥራ በመሥራት አይደ
ለም፤ በእግዚአብሔር ቃል፥ እርሱንም በማ
መን በእውነተኛ ሃይማኖቱ[፩] ይህን አገኘ እንጂ።
፲፬የአሪትን ሕግ የፈጸመ ብቻ ተስፋ የሚያገኝ፥
ዓለምንም የሚወርስ ቢሆን ኖሮ፥ ለአብርሃም
እምነቱ ባልጠቀመውም ነበር፤ ተስፋውንም
ባላገኘም ነበር።[፪] ፲፭የአሪት ሕግ በእፍራሹ ላይ

---

፩ በእግዚአብሔር ቃል እርሱንም በማመን" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ ግሪኩ "እምነት ከንቱ ሆኖአል የተለፋውም ቃል ተሽሮአል" ይላል።

፫፥፲፰ መዝ. ፴፭፥፩። ፫፥፳ መዝ. ፻፵፪፥፪፤ ገላ. ፪፥፲፮። ፫፥፳፪ ገላ. ፪፥፲፮።
፫፥፴ ዘዳ. ፮፥፬፤ ገላ. ፫፥፳። ፬፥፫ ዘፍ. ፲፭፥፮፤ ገላ. ፫፥፮። ፬፥፯-፰ መዝ. ፴፩፥፩-፪። ፬፥፲፩ ዘፍ. ፲፯፥፲።
፬፥፲፫ ዘፍ. ፲፯፥፬-፮፤ ፳፪፥፲፯-፲፰፤ ገላ. ፫፥፳፱። ፬፥፲፬ ገላ. ፫፥፲፰።

ቅጣትን ያመጣልና፤ የኦሪት ሕግም ከሌለ መተ
ላለፍ የለም።
፲፮ስለዚህም እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ
የሰጠው ተስፋ የታመነ ይሆን ዘንድ፥ የሚጸ
ድቁ በእምነት እንጂ የኦሪትን ሥራ በመፈጸም
ብቻ እንዳይደለ ያውቁ ዘንድ እግዚአብሔር
ጽድቅን በእምነት አደረገ። ፲፯"ለብዙዎች አሕ
ዛብ አባት አደርግሃለሁ" ተብሎ እንደ ተጻፈ
ሙታንን በሚያስነሣቸው፥ የሌሉትንም እንደ
አሉ በሚያደርጋቸው በአመነበት በእግዚአብ
ሔር ፊት አብርሃም የሁላችን አባት ነው።
፲፰አብርሃም "ዘርህ እንዲሁ ይሆናል" ብሎ
እግዚአብሔር ተስፋ እንደ ሰጠው ተስፋ ባል
ነበረ ጊዜ የብዙዎች አሕዛብ አባት እንደሚ
ሆን አመነ። ፲፱አብርሃም የመቶ ዓመት ሽማግሌ
ስለሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና
የሣራ ማኅፀን ምውት መሆኑን እያየ በእምነት
አልተጠራጠረም። ፳እግዚአብሔር ያናገረለት
ንም ተስፋ ይቀራል ብሎ አልተጠራጠረም፤
በእምነት ጸና እንጂ፤ ለእግዚአብሔርም ክብ
ርን ሰጠ። ፳፩እግዚአብሔርም የሰጠውን ተስፋ
ሊያደርግለት እንደሚችል በፍጹም ልቡ አመነ።
፳፪ስለዚህም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት። ፳፫ነገር
ግን "ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት" የሚለው ቃል
የተጻፈ ስለ እርሱ ብቻ አይደለም። ፳፬-፳፭ስለ
ኀጢአታችን የተሰቀለውን፥ ሊያስነሣንና ሊያ
ጸድቀን የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙ
ታን ለይቶ በአስነሣው ስለምናምን ስለ እኛም
ነው እንጂ።

## ምዕራፍ ፭

### በእምነት ስለ መጽደቅ

፩እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን፥ በእግዚአብ
ሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላ
ምን እናገናለን። ፪በእርሱም አማካኝነት ወደቆ
ምንበት ወደ ጸጋው በእምነት ተመራን፤ በእግ
ዚአብሔርም ክብር ተስፋ እንመካለን። ፫የም
ንመካ በእርስዋ ብቻ አይደለም፤ በመከራችን
ደግሞ እንመካለን እንጂ፤ መከራ በእኛ ላይ
ትዕግሥትን እንደሚያመጣ እናውቃለንና። ፬ትዕ
ግሥትም መከራ ነው፤ በመከራም ተስፋ ይገ
ናል። ፭ተስፋም አያሳፍርም፤ በሰጠን በመን
ፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን
መልቶአልና። ፮ክርስቶስም እኛ ኀጢአተኞች
ስንሆን ስለ ኀጢአታችን ይሞት ዘንድ ዘመኑ
ሲደርስ መጣ።፩ ፯ስለ ክፉዎች በጭንቅ ጊዜ
ስንኳ ቢሆን ሊሞት የሚደፍር አይገኝም፤ ስለ
ደጋጉ ግን ሊሞት የሚጨክን የሚገኝ እንዳለ
እንጃ። ፰እግዚአብሔር ምን ያህል እንደ ወደ
ደን እነሆ፥ እዩ፤ እኛ ኀጢአተኞች ስንሆን
ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ። ፱እንግዲህ በደሙ
ዛሬ ከጸደቅን ከሚመጣው መከራ በእርሱ እን
ድናለን። ፲እኛ የእግዚአብሔር ጠላቶቹ ስን
ሆን በልጁ ሞት ይቅር ካለን፥ ከታረቀን በኋ
ላም በልጁ ሕይወት እንዴት የበለጠ ያድነን!
፲፩በዚህ ብቻ አይደለም፤ በእርሱ ይቅርታውን
ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስም በእ
ግዚአብሔር ዘንድ እንመካለን እንጂ።

### ሞት በአዳም፥ ሕይወትም በክርስቶስ

፲፪ስለዚህም በአንድ ሰው በደል ምክንያት
ኀጢአት ወደ ዓለም ገባች፤ ስለዚችም ኀጢ
አት ሞት ገባ፤ እንደዚሁም ሁሉ ኀጢአትን
ስለ አደረጉ በሰው ሁሉ ላይ ሞት መጣ።
፲፫ኦሪት እስከ መጣች ድረስ ኀጢአት ምን
እንደ ሆነች ሳትታወቅ በዓለም ውስጥ ነበረች፤
ነገር ግን የኦሪት ሕግ ገና ስላልመጣ ኀጢ
አት ተብላ አትቈጠርም ነበር። ፲፬ነገር ግን በአ
ዳም ኀጢአት ምክንያት ከአዳም እስከ ሙሴ
የበደሉትንም ያልበደሉትንም ሞት ገዛቸው፤
ሁሉ በአዳም አምሳል ተፈጥሮአልና፥ አዳምም
ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና።
፲፭ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋው በበደላ
ችን መጠን የሆነብን አይደለም፤ በአንድ ሰው
በደል ብዙዎች ከሞቱ፥ እንግዲህ በእግዚአብ
ሔር ጸጋ፥ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ
ቤዛነት በሰጠን ሀብቱ ሕይወት በብዙዎች ላይ
እንዴት እጅግ ይበዛ ይሆን? ፲፮የእግዚአብሔር
ጸጋው በአንዱ ሰው ኀጢአት መጠን የሆነብን
አይደለም፤ የኀጢአት ፍርድ ከአንድ ሰው
ወጥታ ሁሉ ከተቀጣባት፥ ጸጋው ከበደላችን
እንደ ምን ያነጻን ይሆን? የዘለዓለምንስ ሕይ
ወት እንዴት ይሰጠን ይሆን?፪ ፲፯የአንዱ ሰው

---

፩ ግሪኩ "ስለ ኀጢአታችን ሞተ" ይላል።
፪ የዘለዓለምንስ ሕይወት እንዴት ይሰጠን ይሆን?" የሚለው በግሪኩ የለም።
፬፥፲፯ ገላ. ፫፥፯። ፬፥፲፯ ዘፍ. ፲፯፥፭። ፬፥፲፰ ዘፍ. ፲፭፥፭። ፬፥፲፱ ዘፍ. ፲፯፥፲፯።
፬፥፳፬-፳፭ ኢሳ. ፶፫፥፬-፭። ፭፥፲፪ ዘፍ. ፫፥፮።

ኀጢአት ሞትን ካነገሠችው በአንድ ሰው በደ
ልም ሞት ከገዛን፥[፫] የአንዱ ሰው የኢየሱስ ክር
ስቶስ የጸጋው ብዛትና የጽድቁ ስጦታ እንዴት
እጅግ ያጸድቀን ይሆን? የዘለዓለም ሕይወትንስ
እንዴት ያበዛልን ይሆን?[፬]
፲፰እንግዲህ በአንዱ ሰው በደል ዓለም ሁሉ
እንደ ተፈረደበት፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ ሰው
ጽድቅ ሰው ሁሉ ይጸድቃል። ፲፱በአንድ ሰው
አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ፥
እንዲሁ ደግሞ በአንድ ሰው መታዘዝ ብዙዎች
ጻድቃን ይሆናሉ። ፳ኦሪትስ ኀጢአትን ታበዛት
ዘንድ መጣች፤ ኀጢአትም ከበዛች ዘንድ የእ
ግዚአብሔር ጸጋ በዛች። ፳፩ኀጢአትም ሞትን
እንደ አነገሠችው እንዲሁ በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጸጋ ጽድቅን ለዘለዓ
ለም ሕይወት ታነግሠዋለች።

## ምዕራፍ ፮

### ከኀጢአት ተለይቶ በክርስቶስ መኖር

፩እንግዲህ ምን እንላለን? የእግዚአብሔር ጸጋ
እንዲበዛ ኀጢአት እንሥራን? አይደለም። ፪ከኀ
ጢአታችን የተለየን እኛ እንግዲህ እንዴት ዳግ
መኛ በእርስዋ ጸንተን መኖር እንችላለን? ፫ነገር
ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን
እኛ ሁላችን በሞቱ እንደ ተጠመቅን ሁላችሁ
ይህን ዕወቁ። ፬በሞቱም እንመስለው ዘንድ ከእ
ርሱ ጋር በጥምቀት ተቀበርን፤ እርሱ ክርስቶስ
በአባቱ ጌትነት ከሙታን እንደ ተነሣ እኛም
እንደ እርሱ በሐዲስ ሕይወት እንኖራለን።
፭በሞቱ ከመሰልነውም በትንሣኤው እንመ
ስለዋለን። ፮ነገር ግን የኀጢአትን ሥጋ ይሽር
ዘንድ ከእርሱ ጋር የተሰቀለው አሮጌው ሰው
ነታችን እንደ ሆነ ይህን እናውቃለን፤ ከእንግ
ዲህ ወዲያ ዳግመኛ ለኀጢአት እንገዛ ዘንድ
እንመለስም። ፯የሞተስ ከኀጢአት ነጻ ወጥቶ
አል። ፰ከክርስቶስ ጋር ከሞትንም ከእርሱ ጋር
በሕይወት እንደምንኖር እናምናለን። ፱ክርስቶስ
ከሙታን ተለይቶ እንደ ተነሣ፥ ዳግመኛም እን
ደማይሞት፥ እንግዲህ ወዲህም ሞት እንደማይ
ገዛው እናውቃለን። ፲የሞተ አንድ ጊዜ ሞተ፤
በሞቱም ኀጢአትን ሻራት፤ የተነሣም ለእግ
ዚአብሔር ተነሣ። ፲፩እንዲሁ እናንተም ራሳ
ችሁን ለኀጢአት ምውታን አድርጉ፤ በጌታ
ችን በኢየሱስ ክርስቶስም ለእግዚአብሔር ሕያ
ዋን ሁኑ።
፲፪በዚህ በሚሞት ሰውነታችሁ ኀጢአትን አታ
ንግሡአት፤ ለምኞቱም እሽ አትበሉት። ፲፫ከሙ
ታን ተለይቶ እንደ ተነሣ፥ ራሳችሁን ለእግዚእ
ብሔር መሥዋዕት አድርጉ እንጂ ሰውነታችሁን
ለኀጢአት የዐመፅ የጦር መሣሪያ አታድርጉት፤
ሰውነታችሁንም ለእግዚአብሔር የጽድቅ የጦር
መሣሪያ አድርጉ። ፲፬እንግዲህ ኀጢአት አትገዛ
ችሁም፤ የኦሪትን ሕግ ከመሥራት ወጥታችሁ
ወደ እግዚአብሔር ጸጋ ገብታችኋልና።

ስለ መታዘዝ ምሥጢር

፲፭እንግዲህ ምን እንላለን? የኦሪትን ሕግ ከመ
ሥራት ወጥተን ወደ እግዚአብሔር ጸጋ ስለ
ገባን ኀጢአት እንሥራን? አይደለም። ፲፮ለም
ትታዘዙለት፥ እሺ ለምትሉትም እናንተ አገል
ጋዮች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ለተባበራ
ችሁለትስ ራሳችሁን እንደ አስገዛችሁ አታው
ቁምን? ኀጢአትንም እሺ ብትሉአት፥ ተባ
ብራችሁም ብትበድሉ እናንተ ለሞት ተገዢ
ዎች ትሆናላችሁ፤ ጽድቅንም እሺ ብትሉአት
ለበጎ ሥራም ብትተባበሩ የእግዚአብሔር አገል
ጋዮች ናችሁ። ፲፯የኀጢአት ተገዦች ስትሆኑ
ምሳሌነቱ ለተሰጣችሁ ለምትማሩት ትምህርት
ታዝዛችኋልና እግዚአብሔር ይመስገን። ፲፰አሁን
ግን ከኀጢአት ነጻ ሁናችሁ ለጽድቅ ተገዝታች
ኋል። ፲፱ስለ ሰውነታችሁ ድካም በሰው ልማድ
እነግራችኋለሁ፤ ዕወቁ፤ ቀድሞ ሰውነታችሁን
ለኀጢአትና ለርኵሰት፥ ለዐመፃም እንደ አስገ
ዛችሁ፥ እንዲሁ አሁንም ሰውነታችሁን ለጽድ
ቅና ለቅድስና አስገዙ። ፳ለኀጢአት ትገዙ በነ
በረበት ጊዜ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና። ፳፩በዚ
ያን ጊዜ ሥራችሁም እነሆ፥ ዛሬ ታፍሩበታላ
ችሁ፤ መጨረሻው ሞት ነውና። ፳፪ዛሬ ግን
ከኀጢአት ነጻ ወጣችሁ፤ ራሳችሁንም ለጽድቅ
አስገዛችሁ፤[፭] ለቅድስናም ፍሬን አፈራችሁ፤
ፍጻሜውም የዘለዓለም ሕይወት ነው። ፳፫የኀ
ጢአት ትርፍዋ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር

፫ "በአንድ ሰው በደል ሞት ከገዛን" የሚለው በግሪኩ የለም።
፬ "የዘለዓለም ሕይወትንስ እንዴት ያበዛልን ይሆን" የሚለው በግሪኩ የለም።
፭ በግሪኩ "ለእግዚአብሔር ተገዛችሁ" ይላል።
፮፥፬ ቆላ. ፪፥፲፪። ፮፥፮ ገላ. ፪፥፳። ፮፥፯ ፩ ጴጥ. ፬፥፩። ፮፥፰ ፪ ጢሞ. ፪፥፲፩። ፮፥፱ ራእ. ፩፥፲፰።
፮፥፳፩ ምሳ. ፲፬፥፲፪፤ ሕዝ. ፴፮፥፴፩።

ጸጋ ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘለዓ
ለም ሕይወት ነው።

## ምዕራፍ ፯

፩ወንድሞቻችን! ሕግን ለሚያስተውሉ እና
ገራለሁና፥ ሰው በሕይወት ባለበት ሁሉ ሕግ
እንዲገዛው አታውቁምን? ፪ባል ያላት ሴት
ባልዋ በሕይወት ሳለ ከእርሱ ጋር በሕግ የታሰ
ረች ናት፤ ባልዋ የሞተ እንደ ሆነ ግን በሚስት
ነት ታስራበት ከኖረችው ሕግ የተፈታች ናት።
፫ስለዚህ ባልዋ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ
ብትሆን አመንዝራ ትሆናለች፤ ባልዋ ቢሞት
ግን ከሕግ ነጻ ወጥታለች፤ ለሌላ ወንድ ብትሆ
ንም አመንዝራ አትባልም።
፬ወንድሞች ሆይ! እናንተ እንዲሁ የክርስ
ቶስ አካል ስለ ሆናችሁ ከኦሪት ተለይታች
ኋል፤ ለእግዚአብሔርም ፍሬ እንድታፈሩ ከሙ
ታን ተለይቶ ለተነሣው ለዳግማዊ አዳም ሆና
ችኋል። ፭የሰውን ሕግ በሠራን ጊዜ ግን በኦ
ሪት ሕግ ደካማነት ቅጣቱ ጸናብን፤ ሞትንም
እፈራን።[፩] ፮አሁን ግን ታስረንበት ከነበረው
ከኦሪት ሕግ ነጻ ወጥተናል፤ ስለዚህ በብሉይ
መጽሐፍ ሳይሆን በአዲሱ መንፈሳዊ ሕይወት
እንገዛለን።

### ኦሪትን ስለ መተው

፯እንግዲህ ምን እንላለን? ኦሪት ኀጢአት
ናትን? አይደለችም፤ ነገር ግን ኦሪት ባትሠራ
ኀጢአትን ባላወቅኋትም ነበር፤ ኦሪት፥ "አት
መኝ" ባትል ኖሮም ምኞትን ፈጽሞ ባላወቅኋ
ትም ነበር። ፰ያችም ትእዛዝ ለኀጢአት ምክን
ያት ሆነቻት፤ ምኞትንም ሁሉ አመጣችብኝ፤
ቀድሞ ግን ኦሪት ሳትሠራ ኀጢአት ሙት ነበ
ረች። ፱እኔም ቀድሞ ኦሪት ሳትሠራ ሕያው ነበ
ርሁ፤ የኦሪት ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኀጢ
አት ሕይወትን አገኘች፤ እኔ ግን ሞትሁ።
፲ለሕይወት የተሠራችልኝ ያቺ ሕግ ለሞት ሆና
አገኘኋት። ፲፩ኀጢአት በዚያች ትእዛዝ ምክን
ያት አሳተችኝ፤ በእርሷም ገደለችኝ። ፲፪አሁ
ንም ቢሆን ኦሪትስ ቅድስት ናት፤ ትእዛዝዋም
ቅዱስና እውነት ነው፤ መልካምም ነው፤ በረ
ከትም ነው።[፪]

፲፫እንግዲህ ያ መልካም ነው ብዬ የማስበው
ነገር በውኑ አጥፊ ሆነኝ እላለሁን? አይደለም፤
ነገር ግን ኀጢአት ኀጢአት እንደ ሆነች በታ
ወቀች ጊዜ ሞትን አበዛችብኝ፤ ከዚያም ትእ
ዛዝ የተነሣ ኀጢአተኛው እንዲታወቅ፥ ኀጢአ
ትም ተለይታ እንድትታወቅ ኦሪት መልካሙን
ከክፉ ልትለይ ተሠርታለች።[፫]

### ስለ መንፈሳዊ ሕግ

፲፬የኦሪት ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለን፤
እኔ ግን ለኀጢአት የተሸጥሁ ሥጋዊ ነኝ። ፲፭የማደ
ርገውን አላውቅምና፤ የምወደውንም ያን ምንም
አላደርገውምና፤ ያንኑ የምጠላውን ብቻ እሠራ
ለሁ እንጂ። ፲፮የማልወደውን የምሠራ ከሆንሁ ግን
ያ የኦሪት ሕግ መሠራት ለበጎ እንደ ሆነ ምስክሩ
እኔ ነኝ። ፲፯እንግዲያስ በእኔ ላይ ያደረች ኀጢ
አት ናት እንጂ፥ ያን የማደርገው እኔ አይደለሁም።
፲፰በእኔ ማለት በሥጋዬ መልካም ነገር እንደማይ
ኖር አውቃለሁ፤ መልካም ሥራ ለመሥራት መሻ
ቱስ በእኔ ዘንድ አለ፤ በጎ ምግባር መሥራት ግን
የለኝም። ፲፱ያን የምወደውንም በጎ ነገር የማደርግ
አይደለም፤ ነገር ግን ያን የምጠላውን ክፉውን
አደርጋለሁ። ፳የማልወደውንስ የምሠራ ከሆን የም
ሠራው እኔ አይደለሁም፤ በእኔ ላይ ያደረች ኀጢ
አት ናት እንጂ። ፳፩መልካም ሥራ እንድሠራ የፈቀ
ደልኝን ያን ሕግ እርሱ ክፉ ነገር አምጥቶብኝ አገ
ኘሁት። ፳፪በልቡናዬ ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር
ሕግ መልካም ነው። ፳፫ነገር ግን በሰውነቴ ውስጥ
ያለውን ሌላ የኀጢአት ሕግ እመለከታለሁ፤ በል
ቡናዬም ውስጥ ካለው ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር
ተሰልፈው ተዋጉ፤ በሰውነቴ ውስጥ ያለው ያ የኀ
ጢአት ሕግም በረታና ወደ እርሱ ማረከኝ። ፳፬እኔ
ምንኛ ወራዳ ሰው ነኝ፤ ከዚህ ሟች ሰውነቴ ማን
ባዳነኝ? ፳፭በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብ
ሔር ይመስገን፤ እኔ በልቤ ለእግዚአብሔር ሕግ
እገዛለሁ፤ በሥጋዬ ግን ለኀጢአት ሕግ እገዛለሁ።

## ምዕራፍ ፰

### የኦሪት ሕግ ሰውን ማዳን እንደ ተሳነው

፩እንግዲህ በኢየሱስ ክርስቶስ ላሉት በመን
ፈስ እንጂ በሥጋ ለማይመላለሱ ፍርድ የለባ

---

፩ ምዕ. ፯ ቍ. ፭ ከግሪኩ ይለያል።
፪ "በረከትም ነው" የሚለው በግሪኩ የለም።
፫ "ኦሪትም መልካሙን ከክፉ ልትለይ ተሠርታለች" የሚለው በግሪኩ የለም።
፯፥፯ ዘፀ. ፳፥፲፯፤ ዘዳ. ፭፥፳፩። ፯፥፲፩ ዘፍ. ፫፥፲፫። ፯፥፲፭ ገላ. ፭፥፲፯።

ቸውም። [፪]በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠን ሕይ
ወት የሚገኝበት የመንፈስ ሕግ እርሱ ከኀጢ
አትና ከሞት ሕግ ነጻ እውጥቶናልና።[፩] [፫]ስለ
ሥጋ ደካማነት የኦሪት ሕግ ከሞት ማዳን በተ
ሳነው ጊዜ እግዚእብሔር በኀጢአተኛ ሥጋ
ምሳሌ ልጁን ላከ፤ ያችንም ኀጢአት በሥጋው
ቀጣት። [፬]እኛን ያጸድቀን ዘንድ፥ የኦሪትንም
ሕግ ሠርቶ እንደ ፈጸመ ሰው ያደርገን ዘንድ፤
ይህም በመንፈሳዊ ሕግ ጸንተው ለሚኖሩ ነው
እንጂ በሥጋ ሕግ ለሚሠሩ እይደለም። [፭]እንደ
ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፤
እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን
ነገር ያስባሉ። [፮]የሥጋ ዐሳብ ሞትን ያመጣብ
ናል፤ የመንፈስ ዐሳብ ግን ሰላምንና ሕይወ
ትን ይሰጠናል። [፯]የሥጋ ዐሳብ ለእግዚእብሔር
ጠላቱ ነውና፤ ለእግዚአብሔርም ሕግ ስለማይ
ገዛ፥ መፈጸም እይቻለውም። [፰]ለሥጋዊ ፈቃዳ
ቸው የሚሠሩ ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ ማሰ
ኘት አይችሉም።

[፱]እናንተ ግን ለመንፈሳዊ ሕግ እንጂ ለሥጋ
ችሁ ፈቃድ የምትሠሩ አይደላችሁም፤ የእግዚ
አብሔር መንፈስ በእናንተ አድሮ ይኖራልና፤
የክርስቶስ መንፈስ ያላደረበት ግን እርሱ የእ
ርሱ ወገን አይደለም። [፲]ክርስቶስ ካደረባችሁ ግን
ሰውነታችሁን ከኀጢአት ሥራ ለዩ፤ መንፈሳች
ሁንም ለጽድቅ ሥራ ሕያው አድርጉ። [፲፩]ጌታ
ችን ኢየሱስን ከሙታን ለይቶ ያስነሣው የእግ
ዚእብሔር መንፈስ ካደረባችሁ ኢየሱስ ክርስ
ቶስን ከሙታን ለይቶ ያስነሣው እርሱ አድሮባ
ችሁ ባለ መንፈሱ ለሟች ሰውነታችሁ ሕይወ
ትን ይሰጣታል።

*ሥጋዊ ሥራን ማዘውተር የማይገባ ስለ መሆኑ*

[፲፪]ወንድሞቻችን፥ አሁንም በሥጋችን ሳለን
በሥጋ ፈቃድ እንኖር ዘንድ አይገባም። [፲፫]እንደ
ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞታላችሁ፤ ነገር ግን
በመንፈሳዊ ሥራ የሥጋችሁን ፈቃድ ብትገድሉ
ለዘለዓለም በሕይወት ትኖራላችሁ። [፲፬]በእግዚአ
ብሔር መንፈስ የሚሠሩ ሁሉ የእግዚአብሔር
ልጆች ናቸው። [፲፭]ዳግመኛም አባ አባት ብለን
የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ
እንጂ እንደ ገና ለፍርሀት የባርነት መንፈስን አል
ተቀበላችሁምና። [፲፮]እኛ የእግዚአብሔር ልጆች
እንደሆን ለልቡናችን ምስክሩ እርሱ መንፈስ
ቅዱስ ነው። [፲፯]እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆን
ወራሾቹ ነን፤ የእግዚአብሔር ወራሾች ከሆንም
የክርስቶስ ወራሾቹ ነን፤ በመከራ ከመሰልነውም
በክብር እንመስለዋለን።

## ስለ መንግሥተ ሰማያት

[፲፰]ነገር ግን የዚህ ዓለም መከራ ለእኛ ሊገለጥ
ከአለው ክብር ጋር እንደማይተካከል ዐስቡ።
[፲፱]የዓለም ተስፋው የእግዚአብሔርን ልጅ[፪] መም
ጣት ይጠባበቅ ነበርና። [፳]ዓለም ባለማወቅ ለከ
ንቱ ነገር ተገዝቶእልና በተስፋ ስለ እስገዛው
ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም። [፳፩]ነገር ግን
እስቶ በባርነት ከሚገዛው ከዚህ ወጥቶ የእግዚ
እብሔር ልጆች ወደ አገኙእት የነጻነት ክብር
ይገባ ዘንድ ተስፋ አለው። [፳፪]እስካሁን ዓለም
ሁሉ ያዘነና የተከዘ እንደ ሆነ እናውቃለን።
[፳፫]ነገር ግን የሚተክዝ ዓለም ብቻ አይደለም፤
የመንፈስ ቅዱስን ፈለማ የተቀበልነው እኛም
ደግሞ እናዝናለን እንጂ፤ የነፍሳችንን ድኅነት
እናገኝ ዘንድ የልጅነትን ክብር ተስፋ እናደር
ጋለንና፤ በእምነትም ድነናልና። [፳፬]የሚታየውን
ተስፋ ማድረግ ተስፋ እይደለም፤ የሚያየው
ንማ እንዴት ተስፋ ያደርጋል? እንዴትስ ይጠ
ብቃል?[፫] [፳፭]የማይታየውን ተስፋ ብናደርግ ግን
እርሱን ተስፋ እድርገን በእርሱ እንደ ጸናን
መጠን[፬] ትዕግሥታችን ይታወቃል። [፳፮]መንፈስ
ቅዱስም ከድካማችን ይረዳናል፤ እንግዲያስ ተስ
ፋችንን ካላወቅን ጸሎታችን ምንድነው? ነገር
ግን እርሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ስለ መከራችንና
ስለ ችግራችን ይፈርድልናል።[፭] [፳፯]እርሱም ልባ
ችንን ይመረምራል፤ ልብ የሚያስበውንም እርሱ
ያውቃል፤ ስለ ቅዱሳንም በእግዚአብሔር ዘንድ

---

፩ እንዳንድ የግሪክ ምንባብ "ነጻ እውጥቶናል" ይላል።

፪ ግሪኩ"የእግዚአብሔር ልጆች" ይላል።

፫ "እንዴትስ ይጠብቃል" የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ "እርሱን ተስፋ እድርገን በእርሱ እንደ ጸናን መጠን" የሚለው በግሪኩ የለም።

፭ ምዕ. ፰ ቍ. ፳፮ በግእዙና በግሪኩ ሰፊ ልዩነት አለ።

፰፥፲፩ ፩ቆሮ. ፫፥፲፮። ፰፥፲፭ ማር. ፲፬፥፴፮፤ ገላ. ፬፥፮። ፰፥፲፭-፲፯ ገላ. ፬፥፭-፯። ፰፥፳ ዘፍ. ፫፥፲፯-፲፱።
፰፥፳፫ ፪ቆሮ. ፭፥፪-፬።

ይፈርዳል።[፭] ፳፰እግዚአብሔር የሚወዱትን ምር
ጦቹን በበጎ ምግባር ሁሉ እንደሚረዳቸው እና
ውቃለን። ፳፱ልጁ በብዙዎች ወንድሞች መካከል
በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸውንና የመ
ረጣቸውን እነርሱን ልጁን ይመስሉ ዘንድ አዘ
ጋጅቶአቸዋል። ፴ያዘጋጃቸውን እነርሱን ጠራ፤
የጠራቸውንም እነርሱን አጸደቀ፤ የአጸደቃቸው
ንም እነርሱን አከበረ።

፴፩እንግዲህ ስለዚህ ምን እንላለን? እግዚአብ
ሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይችለናል?[፮] ፴፪ለልጁ
ስንኳ አልራራም፤ ስለ ሁላችን ቤዛ አድርጎ አሳ
ልፎ ሰጠው እንጂ፥ እንግዲህ እርሱ ሁሉን እን
ዴት አይሰጠንም? ፴፫እንግዲህ እርሱ ራሱ ካጸ
ደቀ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰዎች የሚቃ
ወማቸው ማን ነው? ፴፬የሚፈርድስ ማን ነው?
የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን ተለይቶ የተነ
ሣው፥ በእግዚአብሔርም ቀኝ የተቀመጠው፥
ደግሞ ስለ እኛ የሚፈርደው[፯] ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ነው። ፴፭ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?
መከራ ነውን? ኀዘን ነውን? ስደት ነውን?
ራብ ነውን? መራቆት ነውን? ጭንቀት ነውን?
ሾተል ነውን? ፴፮መጽሐፍ እንዳለ፥ "ስለ አንተ
ዘወትር ይገድሉናል፤ እንደሚታረዱ በጎችም
ሆነናል።" ፴፯ነገር ግን በወደደን በእርሱ ሁሉን
ድል እንነሣለን። ፴፰ነገር ግን ሞትም ቢሆን፥
ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ አለቆ
ችም ቢሆኑ፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም
ቢሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ካለ ከእግ
ዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንደማይችል አምና
ለሁ። ፴፱ኀይልም ቢሆን፥ ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅ
ታም ቢሆን፥ ሌላ ፍጥረትም ቢሆን ከክርስቶስ
ፍቅር ሊለየን የሚችል የለም።

## ምዕራፍ ፱

### እግዚአብሔር እስራኤልን እንደ መረጠ

፩በክርስቶስ እውነት እነግራችኋለሁ፤ ሐሰ
ትም አልናገርም። ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ
ይመሰክርልኛል፤ ፪በጊዜው ሁሉ ብዙ ኀዘን፥
የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለ። ፫በሥጋ
ዘመዶቼና ወንድሞቼ ስለሚሆኑ እኔ ከክርስ
ቶስ እለይ ዘንድ እጸልያለሁ። ፬እኒህም ልጅ
ነት፥ ክብር፥ ኪዳን፥ ሕግና አምልኮ ያላቸው፥
ተስፋም የተሰጣቸው እስራኤላውያን ናቸው።
፭እነርሱም አባቶቻችን ናቸው፤ ከእነርሱም ክር
ስቶስ በሥጋ ተወለደ፤ እርሱም ከሁሉ በላይ
የሆነ ለዘለዓለም ቡሩክ አምላክ ነው፤ አሜን።

፮ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል አይታበ
ልም፤ እስራኤል ሁሉ እስራኤላውያን አይ
ደሉምና። ፯የአብርሃም ዘር ሁሉ ልጆቹ የሆ
ኑት አይደለም፤ ከይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል
አለው እንጂ። ፰ልጆች እንዲሆኑት ተስፋ ያና
ገረለት የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፤ እነዚህ
ከሥጋ የተወለዱ ግን የእግዚአብሔር ልጆች
አይደሉም። ፱"ከርሞ እንደ ዛሬ ወደ አንተ
እመለሳለሁ፤ ሣራም ወንድ ልጅ ታገኛለች፤"
ብሎ ተስፋ ሰጥቶታልና። ፲ነገር ግን ለእርስዋ
ብቻ አይደለም፤ ርብቃም ለአባታችን ለይስ
ሐቅ መንታ በፀነሰች ጊዜ፥ ፲፩ሳይወለዱ፥ ከፉና
መልካም ሥራም ሳይሠሩ የእግዚአብሔር መም
ረጡ በምን እንደ ሆነ ይታወቅ ዘንድ፥ ፲፪እርሱ
የጠራው ነው እንጂ ሰው በሥራው የሚመረጥ
እንዳይደለም ያውቁ ዘንድ፥ ለርብቃ፥ "ታላቁ
ለታናሹ ይገዛል" አላት። ፲፫"ያዕቆብን ወደ
ድሁ፤ ዔሳውን ግን ጠላሁ" ተብሎ እንዲሁ
ተጽፎአልና። ፲፬እንግዲህ ምን እንላለን? እግ
ዚአብሔር ያደላልን? አያደላም። ፲፭እግዚአብ
ሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፥ "የምምረውን
እምረዋለሁ፤ ይቅር የምለውንም ይቅር እለ
ዋለሁ።" ፲፮አሁንም ስሮጠና ለቀደመ አይደ
ለም፤ እግዚአብሔር ይቅር ላለው ነው እንጂ።
፲፯እግዚአብሔርም ለፈርዖን በመጽሐፍ እንዲህ
አለው፥ "ኀይሌን በአንተ ላይ እገልጥ ዘንድ፥
ስሜም በምድር ሁሉ ይሰማ ዘንድ ስለዚህ አስ
ነሣሁህ።" ፲፰እነሆ፥ የሚወድደውን ይምረዋል፤
የሚወድደውንም ልቡን ያጸናዋል።

፲፱እንግዲህ ምን ትላለህ? አንተ እግዚአብ
ሔርን ትነቅፋዋለህን?[፰] ምክሩንስ የሚቃወማት

---

፭ ግሪኩ "ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ ዐሳብ ምን እንደሆነ ያውቃል፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና" ይላል።

፮ ግሪኩ "ማን ይቃወመናል" ይላል።

፯ ግሪኩ "የሚማልደው" ይላል።

፰ ግሪኩ "እንግዲህ እርሱ እስከ አሁን ድረስ ስለምን ይነቅፋል?" ይላል።

፰፥፴፮ መዝ. ፵፫፥፳፪።  ፱፥፯ ዘፀ. ፱፥፯።  ፱፥፯ ዘፍ. ፳፩፥፲፪።  ፱፥፱ ዘፍ. ፲፰፥፲።  ፱፥፲፪ ዘፍ. ፳፭፥፳፫።
፱፥፲፫ ሚል. ፩፥፪-፫።  ፱፥፲፭ ዘፀ. ፴፫፥፲፱።  ፱፥፲፯ ዘፀ. ፱፥፲፮።

አለን?። ፳ሰው ሆይ፥ እግዚአብሔርን የምትከ
ራከረው አንተ ምንድን ነህ? ሥራ ሠሪውን እን
ዲህ አታድርገኝ ሊለው ይችላልን? ፳፩ሸክላ ሠሪ
ከአንድ ጭቃ ግማሹን ለክብር፥ ግማሹንም ለኀ
ሳር አድርጎ ዕቃን ሊሠራ አይችልምን? ፳፪እግ
ዚአብሔርም ኀይሉን የሚገልጽበትን ቅጣቱን
ሊያሳይ ቢወድ፥ ትዕግሥቱን ካሳየ በኋላ ለማጥ
ፋት የተዘጋጁትን ቍጣውን የሚገልጽባቸውን
መሳእክት[፩] ያመጣል። ፳፫ዳግመኛም የክብሩን
ባለጠግነት ሊያሳይ ቢወድ አስቀድሞ ለወደዳቸ
ውና ለጠራቸው ለይቅርታ የተዘጋጁ የምሕረት
መሳእክትን[፪] ያመጣል። ፳፬ወደ ክብሩ የጠራንና
የሰበሰበንም እኛ ነን፤ ነገር ግን ከአሕዛብም
ነው እንጂ ከአይሁድ ብቻ አይደለም። ፳፭ነቢዩ
ሆሴዕ እንዲህ እንዳለ “ወገኔ ያልነበረውን ወገኔ
አደርገዋለሁ፤ ወዳጄ ያልነበረችውንም ወዳጄ
አደርጋታለሁ። ፳፮የእግዚአብሔር ወገኖች አይ
ደላችሁም ይባሉ በነበሩበት ሀገርም የእግዚአ
ብሔር ልጆች ይሆናሉ።” ፳፯ኢሳይያስም ድም
ፁን ከፍ አድርጎ ስለ እስራኤል እንዲህ አለ፥
“የእስራኤል ልጆች ቍጥራቸው እንደ ባሕር
አሸዋ ቢሆንም የተረፉት ይድናሉ። ፳፰እግዚአ
ብሔር በዓለም ውስጥ ያደርገው ዘንድ ያለውን
ያለቀና የተቈረጠ ነገርን ይናገራልና።” ፳፱ኢሳ
ይያስም አስቀድሞ እንደ ተናገረ “እግዚአብ
ሔር ጸባኦት ዘር ያስቀረልን ባይሆን ኖሮ እንደ
ሰዶም በሆን፥ ገሞራንም በመሰልን ነበር።”

## በእምነት ስለ መጽደቅ

፴እንግዲህ ምን እንላለን? ጽድቅን ያልፈለ
ጉአት አሕዛብ ስንኳ ጽድቅን አገኙአት፤ በእ
ምነትም ጸደቁ። ፴፩እስራኤል ግን ኦሪትን ሲከ
ተሉ መጽደቅ ተሳናቸው፤ የኦሪታቸውን ሥራ
አልፈጸሙምና።[፫] ፴፪ይህስ ስለምን ነው? ጽድ
ቃቸው የኦሪትን ሥራ በመሥራት እንጂ በእ
ምነት ስለ አልሆነ ነው፤ የእንቅፋት ድንጋይ
አሰነካከለቻቸው። ፴፫መጽሐፍ እንዲሁ “በጽ
ዮን የእንቅፋት ድንጋይንና የማሰናከያ ዐለትን
አኖራለሁ፤ ያመነባትም ለዘለዓለም አያፍርም”
ብሎአልና።

## ምዕራፍ ፲

## ስለ ጳውሎስ ፈቃድ

፩ወንድሞቼ፥ የእኔስ የልቤ ምኞት፥ ወደ እግ
ዚአብሔር የማቀርበው ጸሎትም እስራኤል እን
ዲድኑ ነው። ፪ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ ምስክ
ራቸው እኔ ነኝና፤ ነገር ግን ዐውቀው አይደ
ለም። ፫የእግዚአብሔርን ጽድቅ አያውቁአት
ምና በራሳቸው ጽድቅ ጸንተው ሊኖሩ ወደዱ፤
ለእግዚአብሔር ጽድቅ ግን መገዛት ተሳና
ቸው። ፬የኦሪት ጽድቅ ፍጻሜስ ለሚያምኑበት
ሁሉ በክርስቶስ ማመን ነው። ፭ሙሴም “የኦ
ሪትን ጽድቅ መሥራትን የፈጸመ ሁሉ በእ
ርሱ ይጸድቅበታል” አለ። ፮የእምነት ጽድቅ
ግን እንዲህ ይላል፥ “በልብህ ወደ ሰማይ ማን
ይወጣል?” አትበል፤ ከሰማይ የወረደው ክርስ
ቶስ ነው።[፬] ፯“ወደ ጥልቁም ማን ይወርዳል?”
አትበል፤ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ክርስ
ቶስ ነው።[፭] ፰መጽሐፍ እንዲሁ፥ “ቃል ለል
ብህም ለአፍህም ቀርቦልሃል ይል የለምን?”
ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው። ፱ኢየ
ሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግ
ዚአብሔርም ከሙታን ለይቶ እንደ አስነሣው
በልብህ ብታምን ትድናለህ። ፲በልቡ የሚያ
ምን ይጸድቃልና፤ በአፉም የሚመሰክር ይድና
ልና። ፲፩መጽሐፍ፥ “የሚያምንበት ሁሉ አያፍ
ርም” ብሎአል። ፲፪አይሁዳዊንና አረማዊን አል
ለየም፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፥ እግዚ
አብሔር ባለጸጋ ስለሆነ ለለመነው ሁሉ ይበቃ
ልና። ፲፫“የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ
ይድናል።”

፲፬ነገር ግን ያላመኑበትን እንዴት ይጠሩታል?
ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እን
ዴት ይሰማሉ? ፲፭“መልካሙን የምሥራች የሚ
ያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው?”

---

፩ “ቍጣውን የሚገልጽባቸው መላእክት” የሚለው በግሪኩ “የቍጣ መሣሪያዎች” ይላል።

፪ “የምሕረት መላእክት” የሚለው በግሪኩ “የምሕረት መሣሪያዎች” ይላል።

፫ የኦሪታቸውን ሥራ አልፈጸሙም” የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ ግሪኩ “ይህም ክርስቶስን ለማውረድ ነው” ይላል።

፭ ግሪኩ “ይህ ክርስቶስን ከሙታን ለማውጣት ነው” ይላል።

፱፥፳ ኢሳ. ፳፱፥፲፮፤ ፵፭፥፱። ፱፥፳፭ ሆሴዕ ፪፥፳፫። ፱፥፳፮ ሆሴዕ ፩፥፲። ፱፥፳፯-፳፰ ኢሳ. ፲፥፳፪-፳፫።
፱፥፳፱ ኢሳ. ፩፥፱። ፱፥፴፫ ኢሳ. ፳፰፥፲፮። ፲፥፭ ዘሌ. ፲፰፥፭። ፲፥፮-፰ ዘዳ. ፴፥፲፪-፲፬።
፲፥፲፩ ኢሳ. ፳፰፥፲፮። ፲፥፲፫ ኢዩ. ፪፥፴፪። ፲፥፲፭ ኢሳ. ፶፪፥፯።

ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብ
ካሉ? ፲፮ነገር ግን ሁሉም የወንጌልን ትምህ
ርት የሰሙ አይደለም፤ ኢሳይያስም፥ “አቤቱ፥
ምስክርነታችንንስ ማን አመነ? የእግዚአብሔርስ
ክንዱ ለማን ተገለጠ?”፫ ብሎአልና። ፲፯ማመን
ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር
ቃል ነው። ፲፰ነገር ግን እንዲህ እላለሁ፤ በውኑ
እስራኤል ብቻ አልሰሙምን? መጽሐፍ “ነገራ
ቸው በምድር ሁሉ ተሰማ፤ ቃላቸውም እስከ
ዓለም ዳርቻ ደረሰ” ብሎ የለምን? ፲፱እስራኤል
ብቻ አልሰሙምን? ሙሴስ አስቀድሞ እንዲህ
ብሎአቸው የለምን? “እኔ በማያስተውሉ ወገ
ኖች አስቀናችዋለሁ፤ ወገን ባልሆነውም አስ
ቈጣችዋለሁ።” ፳ኢሳይያስም ደፍሮ፥ “ለአል
ፈለጉኝ ተገኘሁ፤ ለአልጠየቁኝም ተገለጥሁላ
ቸው” ብሏል። ፳፩ለእስራኤል ግን “ሁልጊዜ
ከዳተኞችና ወንጀለኞች ወደሆኑት ሕዝብ እጄን
ዘረጋሁ” ብሎአል።

## ምዕራፍ ፲፩

### ለእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር ምሕረት

፩እንግዲህ እላለሁ፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን
ጣላቸውን? አይደለም፤ እኔ ደግሞ ከአብርሃም
ዘር ከብንያም ወገን የሆንሁ እስራኤላዊ ነኝ።
፪እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝቡን
አልጣላቸውም፤ ኤልያስ እስራኤልን ወደ እግ
ዚአብሔር እንዲህ ሲል በከሰሳቸው ጊዜ መጽ
ሐፍ ያለውን አታውቁምን? ፫“አቤቱ፥ ነቢያት
ህን ገደሉ፤ መሠዊያዎችህንም አፈረሱ፤ እኔም
ብቻዬን ቀረሁ፤ ነፍሴንም ይሿታል።” ፬የተገለ
ጠለትስ ምን አለው? “ለጣዖት ያልሰገዱ ሰባት
ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀርቻለሁ።” ፭እንዲሁም
ዛሬ በዚህ ዘመን በጸጋ የተመረጡና በእግዚአ
ብሔር ያመኑ፬ ቅሬታዎች አሉ። ፮በጸጋ ከጸ
ደቁ ግን በሥራቸው አይደለም፤ በሥራም የሚ
ጸድቁ ከሆነ ጸጋ ጸጋ አይባልም።

፯እንግዲህ ምንድን ነው? እስራኤል የፈለ
ገውን አላገኘም። የተመረጠው ግን አግኝቶ
አል፤ የቀሩትም ታወሩ። ፰መጽሐፍ እንዳለ፥
“እስከ ዛሬ ድረስ በዐይናቸው እንዳያዩ በጆ
ሮአቸውም እንዳይሰሙ እግዚአብሔር ደንዛዛ
አእምሮን ሰጣቸው።” ፱ዳዊትም እንዲህ ብሎ
አል፥ “ማዕዳቸው በፊታቸው ወጥመድና እን
ቅፋት፥ መሰናክያና ፍዳም ትሁንባቸው። ፲እንዳ
ያዩ ዐይኖቻቸው ይጨልሙ፤ ዘወትርም ጀርባ
ቸው ይጕበጥ።” ፲፩እንግዲህ እላለሁ፤ ሊወድቁ
ተሰናከሉን? አይደለም፤ ነገር ግን እስራኤል
ይቀኑ ዘንድ እነርሱ በመሰናከላቸው ለአሕዛብ
ድኅነት ሆነ። ፲፪የእነርሱ መሰናከል ለዓለም ባለ
ጸግነት፥ በደላቸውም ለአሕዛብ ባለጸግነት ከሆነ
ፍጹምነታቸውማ እንዴት በሆነ ነበር?

### ስለ አሕዛብ መዳን

፲፫ለእናንተ ለአሕዛብ እናገራለሁ፤ እኔ ለአ
ሕዛብ ሐዋርያቸው እንደ መሆኔ መጠን መል
እክቴን አከብራታለሁ። ፲፬ይህም በዚህ ዘመዶ
ቼን አስቀናቸው እንደ ሆነ፥ ከእነርሱ ወገን
የሆኑትንም አድን እንደ ሆነ ነው። ፲፭የእነ
ርሱ መውጣት ለዓለም ዕርቅ ከሆነ ይልቁ
ንም መመለሳቸው ምን ይሆን? ከሙታን
በመነሣት የሚገኝ ሕይወት ነው። ፲፮እርሾዋ
ቅድስት ከሆነች ቡሆውም እንዲሁ ቅዱስ
ነው፤ ሥርዋ ቅዱስ ከሆነም ቅርንጫፎችዋ
እንዲሁ ቅዱሳን ይሆናሉ። ፲፯ከቅርንጫፎ
ችዋ አንዳንዶቹ ቢሰበሩ የዱር ወይራ የሆ
ንህ አንተን በእነርሱ ፋንታ ተከሉ፤ የእነ
ርሱንም ሥርነት አገኘህ፤ እንደ እነርሱም
ዘይት ሆንህ። ፲፰በቅርንጫፎች ላይ አት
ዡራ፤ ብትኰራ ግን ሥሩ አንተን ይሸከም
ሃል እንጂ አንተ ሥሩን የምትሸከመው አይደ
ለም። ፲፱ቅርንጫፎችዋ ተሰበሩ፤ በእነርሱም
ፋንታ “እኔ የዘይት ቅርንጫፍ ሆንሁ” ትል
ይሆናል። ፳አላመኑምና ተሰበሩ፤ አንተ ግን
ስለ አመንህ ቆመሃል፤ እንግዲህ ፈርተህ ኑር
እንጂ ራስህን ከፍ ከፍ አታድርግ። ፳፩እግዚ
አብሔር በተፈጥሮአቸው ቅርንጫፎች ለነበሩ
ለእነዚያ ከአልራራላቸው ለአንተም አይራ
ራልህም፤ ፳፪እንግዲህ የእግዚአብሔርን ር
ኅራኄውንና ጭካኔውን አስተውል፤ የወደቁ
ትን ቀጣቸው፤ አንተን ግን ይቅር እንዳ
ለህ ብትኖር ማረህ፤ ያለዚያ ግን አንተም

---

፫ “የእግዚአብሔርስ ክንዱ ለማን ተገለጠ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ “በእግዚአብሔር ያመኑ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፥፲፮ ኢሳ. ፶፫፥፩። ፲፥፲፰ መዝ. ፲፰፥፬። ፲፥፲፱ ዘዳ. ፴፪፥፳፩። ፲፥፳ ኢሳ. ፷፭፥፩።
፲፥፳፩ ኢሳ. ፷፭፥፪። ፲፩፥፩ ፊል. ፫፥፭። ፲፩፥፫ ፩ነገ. ፲፱፥፲፤ ፲፬። ፲፩፥፬ ፩ነገ. ፲፱፥፲፰።
፲፩፥፰ ዘዳ. ፳፱፥፬፤ ኢሳ. ፳፱፥፲። ፲፩፥፱-፲ መዝ. ፷፰፥፳፪-፳፫።

ትቈረጣለህ። ፳፫እነርሱም ባለማመናቸው ጸን
ተው ባይኖሩ ይተከላሉ። እግዚአብሔር ዳግ
መኛ ሊተክላቸው ይችላልና። ፳፬አንተ የዱር
ወይራ፥ አንተን ስንኳ ከበቀልህበት ቈርጦ
ባልበቀልህበት በመልካሙ ዘይት ስፍራ ከተ
ከለህ፥ ይልቁን ጥንቱን ዘይት የነበሩትን እነ
ዚያን በበቀሉበት ስፍራ እንዴት አብልጦ
ሊተክላቸው አይችልም?

## ስለ እስራኤል መመለስ

፳፭ወንድሞቻችን፥ እኛ ዐዋቂዎች ነን እንዳ
ትሉ ይህን ምሥጢር ልታውቁ እወዳለሁ፦
አሕዛብ ሁሉ እስኪገቡ ድረስ ከእስራኤል
እኩሌቶችን የልብ ድንቍርና አግኝቶአቸዋ
ልና። ፳፮ከዚህ በኋላም መላው እስራኤል
ይድናሉ፤ መጽሐፍ እንዲህ እንዳለ፥ “አዳኝ
ከጽዮን ይወጣል፤ ከያዕቆብም ኀጢአትን
ያስወግዳል። ፳፯ኀጢአታቸውንም ባራቅሁላ
ቸው ጊዜ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን
ይህ ነው።” ፳፰በወንጌል በኩል ስለ እና
ንተ ጠላቶቻችን ናቸው፤ በምርጫ በኩል
ግን ስለ አባቶች ወዳጆች ናቸው። ፳፱በእግ
ዚአብሔር ጸጋና በመጥራቱ ጸጸት የለምና።
፴ቀድሞ እናንተ እግዚአብሔርን እንደ አል
ታዘዛችሁት፥ ዛሬ ግን በእነርሱ አለመታ
ዘዝ ይቅር እንዳላችሁ፥ ፴፩እንዲሁም እና
ንተ በተማራችሁት ምሕረት እነርሱ ምሕረ
ትን እንዲያገኙ እነርሱ ዛሬ አልታዘዙትም።
፴፪እግዚአብሔር ሁሉን ይቅር ይለው ዘንድ
ሁሉን በኀጢአት ውስጥ ዘግቶታልና። ፴፫የእ
ግዚአብሔር ባለጠግነት፥ ጥበብና ዕውቀት
እንዴት ጥልቅ ነው! ለመንገዱም ፍለጋ
የለውም፤ ፍርዱንም የሚያውቀው የለም።
፴፬“የእግዚአብሔርን ዐሳቡን ማን ያውቃል?
ወይስ ማን ተማከረው? ፴፭ብድሩን ይከፍል
ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ ማን አበደረው?”
፴፮ሁሉ ከእርሱ፥ በእርሱና ለእርሱ ነውና፤
ለእርሱም ለዘለዓለም ክብር ምስጋና ይሁን።
አሜን።

## ምዕራፍ ፲፪

## በክርስቶስ ሐዲስ ሕይወት

፩ወንድሞቻችን፥ ሰውነታችሁን ለእግዚአብ
ሔር ሕያውና ቅዱስ፥ ደስ የሚያሰኝም መሥ
ዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአ
ብሔር ርኅራኄ እማልዳችኋለሁ። ይህም በዕ
ውቀት የሚሆን አገልግሎታችሁ ነው። ፪ይህን
ዓለም አትምሰሉ፤ ልባችሁንም አድሱ፤ እግዚ
አብሔር የሚወደውን መልካሙንና እውነቱን፥
ፍጹሙንም መርምሩ።

፫በተሰጠኝ በእግዚአብሔር ጸጋ ሁላችሁም
እንዳትታበዩ እነግራችኋለሁ፤ ራሳችሁን ከዝ
ሙት የምታነጹበትን ዐስቡ እንጂ[፩] ትዕቢትን
አታስቡ፤ ሁሉም እንደ እምነቱ መጠን እግዚ
አብሔር እንደ አደለው ይኑር። ፬በአንዱ ሰውነ
ታችን ብዙ የአካል ክፍሎች እንዳሉ፥ ሥራቸ
ውም ልዩ ልዩ እንደ ሆነ፥ ፭እንዲሁ ሁላችን
ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፤
እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው አካ
ሎች ነን፤[፪] ስጦታውም ልዩ ልዩ ነው፤ ፮እግዚ
አብሔርም በሰጠን ጸጋ መጠን ልዩ ልዩ ስጦታ
አለን። ትንቢት የሚናገር እንደ እምነቱ መጠን
ይናገር። ፯የሚያገለግልም በማገልገሉ ይትጋ፤
የሚያስተምርም በማስተማሩ ይትጋ፤ ፰የሚመ
ክርም በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥም በልግስና
ይስጥ፤ የሚገዛም በትጋት ይግዛ፤ የሚመጸው
ትም በደስታ ይመጽውት።

## ስለ ልዩ ልዩ በጎ ምግባር

፱ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፤ ከከፉ
ራቁ፤ በጎውንም ያዙ፤ ለጽድቅ አድሉ፤[፫]
፲እርስ በርሳችሁ በወንድማማችነት መዋደድ
ተዋደዱ፤ የምትራሩም ሁኑ፤[፬] እርስ በርሳችሁ
ተከባበሩ፤ መምህሮቻችሁንም አክብሩ።[፭]
፲፩ስራ ከመትጋት አትስነፉ፤ በመንፈስ ሕያ
ዋን ሁኑ፤ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ፲፪በተስፋ
ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ታገሡ፤ ለጸሎት

---

፩ “ራሳችሁን ከዝሙት የምታነጹበትን” የሚለው በግሪኩ የለም።
፪ “እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው አካሎች ነን” የሚለው በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።
፫ “ለጽድቅ አድሉ” የሚለው በግሪኩ የለም።
፬ “የምትራሩም ሁኑ” የሚለው በግሪኩ የለም።
፭ “መምህሮቻችሁንም አክብሩ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፩፥፳፮ ኢሳ. ፶፱፥፳። ፲፩፥፳፯ ኤር. ፴፩፥፴፫-፴፬። ፲፩፥፴፫ ኢሳ. ፶፭፥፰። ፲፩፥፴፬ ኢሳ. ፵፥፲፫።
፲፩፥፴፭ ኢዮብ ፵፩፥፲፩። ፲፩፥፴፮ ፩ቆሮ. ፰፥፮። ፲፪፥፬-፭ ፩ቆሮ. ፲፪፥፲፪። ፲፪፥፮-፰ ፩ቆሮ. ፲፪፥፬-፲፩።

ትጉ። ፲፫በችግራቸው ቅዱሳንን ለመርዳት ተባ
በሩ፤ እንግዳ መቀበልንም አዘውትሩ።
፲፬የሚያሳድዱአችሁን መርቁ፤ መርቁ እንጂ
አትርገሙ። ፲፭ደስ ከሚለው ጋር ደስ ይበላ
ችሁ፤ ከሚያለቅሰው ጋርም አልቅሱ። ፲፮እርስ
በርሳችሁም በአንድ ዐሳብ ተስማሙ፤ ትዕቢትን
ግን አታስቡ፤ ራሱን የሚያዋርደውንም ሰው
ምሰሉ፤ እኛ ዐዋቆች ነን አትበሉ። ፲፯ክፉ ላደ
ረገባችሁም ክፉ አትመልሱለት፤ በሰው ሁሉ
ፊት በጎውን ተነጋገሩ። ፲፰ቢቻላችሁስ ከሰው
ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ፲፱ወንድሞቻችን፥ ራሳ
ችሁ አትበቀሉ፤ ቍጣን አሳልፉት፥ "እኔ እበ
ቀላለሁ፤ እኔ ብድራትን እከፍላለሁ ይላል እግ
ዚአብሔር" ተብሎ ተጽፎአልና። ፳ጠላትህ
ቢራብ አብላው፤ ቢጠማም አጠጣው፤ ይህን
ብታደርግ የእሳት ፍሕም በራሱ ላይ ትከምራ
ለህ። ፳፩ክፋውን በመልካም ሥራ ድል ንሣው
እንጂ ክፋውን በክፉ ድል አትንሣው።፲

## ምዕራፍ ፲፫

### ስለ መታዘዝ

፩ሰው ሁሉ በበላይ ላሉ ባለሥልጣኖች ይገዛ፤
ከእግዚአብሔር ከአልተገኘ በቀር ሥልጣን የለ
ምና፤ ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር
የተሾሙ ናቸው። ፪ለባለሥልጣን አልገዛም ያለ
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንቢ ማለቱ ነው፤
መገዛትን እንቢ የሚሉም በራሳቸው ላይ ቅጣ
ትን ያመጣሉ። ፫ሹሞች ሥራው ክፉ ለሆነ
ሰው እንጂ መልካም ለሚሠራ የሚአስፈሩ አይ
ደሉም፤ ሹሞችን እንዳትፈራ ብትፈልግ መል
ካም አድርግ፤ እነርሱ ደግሞ ያመሰግኑሃል፤
፬አንተ ሥራህን ታሳምር ዘንድ የእግዚአብሔር
መልእክተኞች ናቸውና። ክፉ ብታደርግ ግን
ፍራ፤ ሰይፍ የታጠቁም ለከንቱ አይደለም፤
ክፉ አድራጊዎችን ለመቅጣት የእግዚአብሔር
አገልጋዮች ናቸውና። ፭ስለዚህ ቍጣን ስለ
መፍራት ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ስለ ሕሊና
ደግሞ መገዛት ግድ ነው። ፮ስለዚህም ግብር
ታገቡላቸዋላችሁ፤ ለዚህ ሥራ የተሾሙ የእግ
ዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና፤ ፯ለሁሉም እን
ደሚገባው አድርጉ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን
ስጡ፤ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን ስጡ፤ ዐሥራት
ለሚገባው ዐሥራትን ስጡ፤፲፩ ሊፈሩት የሚገባ
ውን ፍሩ፤ ክብር የሚገባውንም አክብሩ።

### ባልንጀራን ስለ መውደድ

፰እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም
ዕዳ አይኑርባችሁ፤ ባልንጀራውን የወደደ ግን
ሕግን ሁሉ ፈጸመ። ፱በኦሪት እንዲህ ብሎአ
ልና፥ "አታመንዝር፤ አትግደል፤ አትስረቅ፤
በሐሰት አትመስክር፥ አትመኝ፤" ደግሞ ሌላ
ትእዛዝ አለ፤ ነገር ግን የሁሉም ራስ " ባልን
ጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" የሚለው ነው።
፲ባልንጀራዉን የሚወድ በባልንጀራዉ ላይ ክፉ
ሥራ አይሠራም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ
ነው። ፲፩ከእንቅልፍ የምትነቁበት ጊዜ እንደ
ደረሰ ዕወቁ፤ ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳና
ችን ዛሬ ወደ እኛ ደርሳለችና። ፲፪ሌሊቱ አል
ፎአል፤ ቀኑም ቀርቦአል። እንግዲህ የጨለማን
ሥራ ከእኛ እናርቅ፤ የብርሃንንም ጋሻ ጦር እን
ልበስ። ፲፫በቀን እንደሚሆን በጽድቅ ሥራ እን
መላለስ፤ በዘፈንና በስካር፥ በዝሙትና በመዳራ
ትም አይሁን፤ በክርክርና በቅናትም አይሁን።
፲፬ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበ
ሱት፤ የሥጋችሁንም ምኞት አታስቡ።

## ምዕራፍ ፲፬

### ባልንጀራን ስለ ማጽናናት

፩እምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው ታገሡት፤
በዐሳቡም አትፍረዱ። ፪ሁሉን ይበላ ዘንድ
እንደ ተፈቀደለት የሚያምን ሁሉን ይብላ፤
የሚጠራጠር ግን አትክልት ይብላ። ፫የሚበላ
ውም የማይበላውን አይናቀው፤ የማይበላውም
የሚበላውን አይንቀፈው፤ ሁሉንም እግዚአብ
ሔር አውቆአቸዋልና።፲፪ ፬እንግዲህ የሌላውን
ሎሌ የምትነቅፍ አንተ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም
ወይም ቢወድቅ ለጌታው ነው። ነገር ግን እግዚ
አብሔር ሊያነሣው ይችላልና ይቆማል።

---

፲ ግሪኩ "በክፉ አትሸነፍ" ይላል።

፲፩ "ዐሥራት ለሚገባው ዐሥራትን ስጡ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፪ ግሪኩ "ተቀብሎታልና" ይላል።

፲፪፥፲፬ ማቴ. ፭፥፵፬፤ ሉቃ. ፮፥፳፰። ፲፪፥፲፯ ምሳ. ፫፥፯። ፲፪፥፲፱ ዘዳ. ፴፪፥፴፭።
፲፪፥፳ ምሳ. ፳፭፥፳፩-፳፪። ፲፫፥፯-፯ ማቴ. ፳፪፥፳፩፤ ማር. ፲፪፥፲፯፤ ሉቃ. ፳፥፳፭።
፲፫፥፱ ዘፀ. ፳፥፲፫-፲፭፤ ፲፯፤ ዘዳ. ፭፥፲፯-፲፱፤ ፳፩፤ ዘሌ. ፲፱፥፲፰።

፭ከቀን ቀን የሚከለከል አለና፤ ዘወትርም
የሚከለከል አለና፤ ነገር ግን ሁሉም ልቡ እንደ
ወደደ ያድርግ።፩ ፮አንዳንድ ቀን የተከለከለም
ለእግዚአብሔር ተከለከለ፤፪ ዘወትር የተከለከ
ለም ለእግዚአብሔር ተከለከለ፤፫ የበላም ለእ
ግዚአብሔር በላ፤ እግዚአብሔርንም ያመሰግ
ነዋል፤ ያልበላም ለእግዚአብሔር አልበላም፤
እግዚአብሔርንም ያመሰግነዋል። ፯ከመካከላች
ንም ለራሱ የሚኖር፥ ለራሱም የሚሞት የለም።
፰በሕይወት ብንኖርም ለእግዚአብሔር እንኖራ
ለን፤ ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን፤
እንግዲህ በሕይወት ብንኖርም ብንሞትም ለእ
ግዚአብሔር ነን። ፱ስለዚህ ሕያዋንንና ሙታንን
ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞተ፥ ተነሣም።
፲እንግዲህ በወንድምህ ላይ የምትፈርድ አንተ
ምንድን ነህ? ወንድምህንስ የምትነቅፍ አንተ
ምንድን ነህ? ሁላችን በክርስቶስ፬ የፍርድ
ዙፋን ፊት እንቆማለንና። ፲፩እግዚአብሔር እን
ዲህ ብሎአልና፥ "እኔ ሕያው ነኝ፤ ጕልበ
ትም ሁሉ ለእኔ ይሰግዳል፤ አንደበትም ሁሉ
ለእኔ ይገዛል።" ፲፪እነሆ፥ ሁላችን በእግዚአብ
ሔር ዘንድ እንደምንመረመር ታወቀ።

## ለባልንጀራ ዕንቅፋት ስላለመሆን

፲፫እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በርሳችን እን
ነቃቀፍ፤ ይልቁንም ለወንድም እንቅፋትን
ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖር ይህን
ዐስቡ። ፲፬በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር እንደሌለ በጌ
ታችን በኢየሱስ ሆኜ ዐውቄአለሁ፤ ተረድቼአ
ለሁም፤ ነገር ግን ማናቸውም ነገር ርኩስ እን
ደሚሆን ለሚያስብ ያ ለእርሱ ርኩስ ነው።
፲፭በመብል ምክንያት ባልንጀራህን የምታሳዝን
ከሆንህ ፍቅር የለህም፤ በውኑ ክርስቶስ ስለ
እርሱ የሞተለት ያ ሰው በመብል ምክንያት
ሊጐዳ ይገባልን? ፲፮እንግዲህ ጌታችን የሰጠንን
መልካሙን ነገር አታስድቡ። ፲፯የእግዚአብሔር
መንግሥት ጽድቅና ሰላም፥ በመንፈስ ቅዱስም
የሆነ ደስታ ነው እንጂ መብልና መጠጥ አይ
ደለምና። ፲፰እንዲህ አድርጎ ለክርስቶስ የሚገዛ
ግን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና በሰውም
ዘንድ የተመረጠ ነው። ፲፱አሁንም ወንድማችን
ይታነጽ ዘንድ ሰላምን እንከተላት።፭ ፳በመብል
ምክንያት የእግዚአብሔርን ፍጥረት አናፍርስ፤
ለንጹሓን ሁሉ ንጹሕ ነው፤ ለሰውስ ክፉው
ነገር በመጠራጠር መብላት ነው። ፳፩ለወንድም
ዕንቅፋት ከመሆን ሥጋን አለመብላት ወይን
ንም አለመጠጣት ይሻላል። ፳፪እምነት ካለህ
በእግዚአብሔር ፊት ባመንኸው እምነት ራስ
ህን አጽና፤ ባገኘው አእምሮም ራሱን የሚዘ
ልፍ ብፁዕ ነው።፮ ፳፫የሚጠራጠር ግን ቢበላ
ይፈረድበታል፤ በማመን አልሆነምና፤ ያለ እም
ነትም የሚደረግ ሁሉ ኀጢአትና በደል ነው።

# ምዕራፍ ፲፭

## ባልንጀራን ስለ መርዳት

፩የሚገባስ እኛ ብርቱዎች ደካሞችን በድካማ
ቸው እንድንረዳቸው ነው፤ ለራሳችንም አናድላ።
፪ሁላችንም በእውነትና በመልካም ሥራ ይታነጽ
ዘንድ ለባልንጀራችን እናድላ። ፫ክርስቶስም፥ "አን
ተን የነቀፉበት ነቀፋ በእኔ ላይ ደረሰ" ብሎ መጽ
ሐፍ እንደ ተናገረ ለራሱ ያደላ አይደለም። ፬የተጻ
ፈው ሁሉ በመታገሣችንና መጻሕፍትን በመታመ
ናችን ተስፋችንን እናገኝ ዘንድ እኛ ልንማርበት
ተጻፈ። ፭የትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ እግ
ዚአብሔር እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ እርስ
በርሳችን አንድ ዐሳብ መሆንን ይስጠን። ፮ሁላችን
አንድ ሆነን በአንድ አፍ በጌታችን በኢየሱስ ክርስ
ቶስ እግዚአብሔርን እናመሰግነው ዘንድ።፯

## ወንጌልን ለአሕዛብም ለአይሁድም ስለ መስበክ

፯አሁንም ባልንጀሮቻችሁን ተቀበሉ፤ ክር
ስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር ተቀብሎአችኋ

---

፩ ምዕ. ፲፬ ቍ. ፭ ከግሪኩ ይለያል።
፪ ግሪኩ "ቀንን የሚያከብር ለጌታ ብሎ ያከብራል" ይላል።
፫ "ዘወትር የተከለከለ ለእግዚአብሔር ተከለከለ" የሚለው በግሪኩ የለም።
፬ አንዳንድ የግሪክ ዘርዕ "በእግዚአብሔር" ይላል።
፭ በግሪኩ "ሰላም የሚቆምበትን እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን እንከተል" ይላል።
፮ ምዕ. ፲፬ ቍ. ፳፪ ግሪኩ "ለአንተ ያለህ እምነት በእግዚአብሔር ፊት ለራስህ ይሁንልህ፤ ፈትኖ መልካም እንደሚ
ሆን በሚቈጥረው ነገር በራሱ ላይ የማይፈርድ ብፁዕ ነው" ይላል።
፯ ምዕ. ፲፭ ቍ. ፭ እና ፮ ግሪኩ በሁለተኛ መደብ ይጽፋል።

፲፬፥፩-፮ ቆላ. ፪፥፲፮። ፲፬፥፲ ፪ቆሮ. ፭፥፲። ፲፬፥፲፩ ኢሳ. ፵፭፥፳፫። ፲፭፥፫ መዝ. ፷፱፥፱።

ልና። ፰እንግዲህ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን
ቃል እውነት ለማድረግ የአባቶቻችንንም ተስፋ
ያጸና ዘንድ ለግዝረት መልእክተኛ ሆነ እላ
ለሁ። ፱አሕዛብም እግዚአብሔርን ያመሰግኑ
ታል፤ ይቅር ብሎአቸዋልና፤ መጽሐፍ እንዲህ
ብሎአልና፥ "እቤቱ፥ ስለዚህ በአሕዛብ መካ
ከል እገዛልሃለሁ፤ ስምህንም አመሰግናለሁ።"
፲ዳግመኛም መጽሐፍ እንዲህ ብሎአል፥ "አሕ
ዛብ ከሕዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ።" ፲፩ዳግመ
ኛም እንዲህ አለ፥ "አሕዛብ ሁላችሁ እግዚአ
ብሔርን አመስግኑ፤ ሕዝቡም ሁሉ ያመስግ
ኑታል።" ፲፪ኢሳይያስም ደግሞ እንዲህ ብሎ
አል፥ "የእሴይ ዘር ይነሣል፤ ከእርሱ የሚነ
ሣውም ለአሕዛብ ንጉሥ ይሆናል፤ ሕዝቡም
ተስፋ ያደርጉታል።" ፲፫የተስፋ አምላክ እግዚ
አብሔርም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በተስፋ ያበ
ዛችሁ ዘንድ በእምነት ደስታንና ሰላምን ሁሉ
ይፈጽምላችሁ።

### የጳውሎስ ሐዋርያዊ ተልእኮ

፲፬ወንድሞቼ ሆይ፥ እኔም በጎ ምግባርን
ሁሉ እንደምትፈጽሙ እታመንባችኋለሁ፤ እና
ንተ ፍጹም ዕውቀትን የተመላችሁ ናችሁ፤
ባልንጀሮቻችሁንም ልታስተምሩአቸው ትችላ
ላችሁ። ፲፭ከእግዚአብሔር ስለ አገኘሁት ጸጋ
ላሳስባችሁ በአንዳንድ ቦታ በድፍረት ጻፍሁ
ላችሁ። ፲፮በአሕዛብ መካከል ኢየሱስ ክርስቶ
ስን አገለግል ዘንድ፥ ስእግዚአብሔር ወንጌልም
እገዛ ዘንድ፥ በእኔ ትምህርት አሕዛብ በመንፈስ
ቅዱስ የተወደደና የተመረጠ መሥዋዕት ይሆኑ
ዘንድ። ፲፯ለእኔም በእግዚአብሔር ዘንድ መመ
ኪያዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ፲፰አሕዛብም
እንዲያምኑ ክርስቶስ በቃልም በሥራም ያደረ
ገልኝን እናገር ዘንድ እደፍራለሁ። ፲፱በኀይልና
በተአምራት፥ በመንፈስ ቅዱስ ኀይልና ድንቅ
ሥራን በመሥራትም፥ ከኢየሩሳሌም አውራጃ
ዎች ጀምሬ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እንደ አስ
ተማርሁ፥ የክርስቶስንም ወንጌል ፈጽሞ እንደ
ሰበክሁ እናገር ዘንድ እደፍራለሁ። ፳ወንጌልን
ለማስተማር ተጋሁ፤ ነገር ግን በሌላ መሠረት
ላይ እንዳላንጽ የክርስቶስ ስም ወደ ተጠራበት
አልሄድሁም። ፳፩"ወሬው ያልደረሳቸው ያው
ቁታል፤ ያልሰሙትም ያስተውሉታል" ብሎ
መጽሐፍ እንደ ተናገረ ነው።
፳፪ዘወትር ወደ እናንተ ልመጣ እወድድ
ነበር፤ ነገር ግን ተሳነኝ። ፳፫አሁን ግን በዚህ
ሀገር ሥራዬን ስለ ጨረስሁ፥ ከብዙ ጊዜም
ጀምሮ ወደ እናንተ ልመጣ እተጋ ስለ ነበር፥
፳፬ወደ እስባንያ ስሄድ እግረ መንገዴን ላያ
ችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ቀደም ብዬ ከእና
ንተ ጋር ደስ ካለኝ በኋላም ከእናንተ ወደዚያ
እሄዳለሁ።

### ምእመናንን ስለ መርዳት

፳፭አሁን ግን ቅዱሳንን ለመርዳት ወደ ኢየ
ሩሳሌም እሄዳለሁ። ፳፮መቄዶንያና አካይያ በኢ
የሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ላሉ ድሆች አስተ
ዋጽኦ ለማድረግ ተባብረዋልና። ፳፯የሚገባቸ
ውም ስለሆነ በመንፈሳዊ ሥራ አሕዛብን ከተ
ባበሩአቸው ለሰውነታቸው በሚያስፈልጋቸው
ሊረዱአቸው ይገባል። ፳፰እንግዲህ ይህን ፍሬ
ጨርሼና አትሜ በእናንተ በኩል ወደ እስባንያ
እሄዳለሁ። ፳፱ነገር ግን በመጨረሻ ጊዜ በክርስ
ቶስ ወንጌል በረከት ፍጹምነት እንደምትመጣ
አምናለሁ።
፴ወንድሞቼ፥ በጸሎታችሁ ስለ እኔ ወደ እግ
ዚአብሔር ከእኔ ጋር ትተጉ ዘንድ በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ፍቅር
እማልዳችኋለሁ። ፴፩ይኸውም በኢየሩሳሌም
ያሉ ቅዱሳንን በአገልግሎቴ ደስ እሰኛቸው
ዘንድ በይሁዳ ሀገር ካሉ ዐላውያን እንዲያድ
ነኝ ነው። ፴፪እግዚአብሔርም ቢፈቅድ በደስታ
ወደ እናንተ መጥቼ ከእናንተ ጋር ዐርፍ ዘንድ
ነው። ፴፫የሰላም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሁን፤
አሜን።

### ምዕራፍ ፲፮

፩ለክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን የምትላላከውን
እኅታችንን ፌቤንን አደራ እላችኋለሁ፤ ፪ለቅዱ
ሳንም እንደሚገባ በጌታችን ተቀበሉአት፤ እር
ስዋ ለብዙዎች፥ ለእኔም ረዳት ናትና፤ ለችግራ
ችሁም በፈቀዳችሁት ቦታ መድቡአት።[፩]
፫በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ከእኔ ጋር የተባበሩ
ትን ጵርስቅላንና አቂላን ሰላም በሉ፤ ፬ስለ እኔ

---

፩ ግሪኩ እና አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "ከእናንተ በምትፈልገው በማንኛውም ነገር ርዱአት" ይላል።

፲፭፥፱ ፪ ሳሙ. ፳፪፥፶፤ መዝ. ፲፰፥፵፱። ፲፭፥፲ ዘዳ. ፴፪፥፵፫። ፲፭፥፲፩ መዝ. ፻፲፯፥፩።
፲፭፥፲፪ ኢሳ. ፲፩፥፲። ፲፭፥፳፩ ኢሳ. ፶፪፥፲፭። ፲፭፥፳፪ ሮም ፩፥፲፫። ፲፭፥፳፭-፳፮ ፩ቆሮ. ፲፮፥፩-፬።
፲፭፥፳፯ ፩ቆሮ. ፱፥፲፩። ፲፮፥፫ ሐ.ሥ. ፲፰፥፪።

ስውነታቸውን ለመከራ አሳልፈው ሰጥተዋልና፤
የማመስግናቸውም እኔ ብቻ አይደለሁም፤ ከአ
ሕዛብ ያመኑ ምእመናን ሁሉ ያመስግኑአቸዋል
እንጂ። ፭በቤታቸው ያሉትን ማኅበረ ክርስቲያ
ንም ሰላም በሉ፤ ወዳጄ ኤጴኔጦስንም ሰላም
በሉ፤ ይኸውም በእስያ በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ
መጀመሪያቸው ነው። ፮ለእናንተ ብዙ የደከመ
ችላችሁን ማርያምንም ሰላም በሉ። ፯ከዘመ
ዶቼ ወገን የሚሆኑትን ከእኔ ጋር ያመኑ እንድ
ራኒቆስንና ዩልያንን ሰላም በሉ፤ ቀደም ሲል
ክርስቶስን እንደ አገለገሉ ሐዋርያት ያውቁአቸ
ዋል። ፰በክርስቶስ ወንድሜ የሆነውን እምጵል
ያጦስን ሰላም በሉ። ፱የክርስቶስን ሥራ በመሥ
ራት የምንተባበረውን ኡሩባኖስን፥ ወዳጄ ስን
ጣክንንም ሰላም በሉ። ፲በክርስቶስ የተመረጠ
ውን ኤጤሌንን ሰላም በሉ፤ እነ አርስጠቦሎስ
ንም ሰላም በሉ። ፲፩ከዘመዶቼ ወገን የሚሆን
ሄሮድዮናን ሰላም በሉ፤ በንርቃሶስ ቤት ያሉ
ትንና በክርስቶስ ያመኑትን ምእመናን ሰላም
በሉ። ፲፪በጌታችን ስም መከራ የተቀበሉትን
የጢሮፌሞናንና የጢሮፌሞስን ወገኖች ሰላም
በሉ። በጌታችን ስም ብዙ የደከመች እኅታች
ንን ጠርሴዳን ሰላም በሉ። ፲፫ጌታችን የመረ
ጠው ሩፎንን፥ እናቱንም፥ ለእኔም እናቴ የሆ
ነችውን ሰላም በሉ። ፲፬አስቀሪጦስን፥ አልሶን
ጳን፥ ሄርሜስን፥ ጳጥሮባስን፥ ሄርማስን፥ ከእነ
ርሱ ጋር ያሉ ወንድሞቻችንንም ሰላም በሉ።
፲፭ፊሎሎጎስን፥ ዩልያን፥ ኔርዮስን፥ እኅቱንም
እሊንጳስን ከእነርሱም ጋር ያሉ ቅዱሳንን ሁሉ
ሰላም በሉ። ፲፮እርስ በርሳችሁ በተቀደሰ ሰላ
ምታ ሰላም ተባባሉ፤ የክርስቶስ ማኅበረ ክርስ
ቲያንም ሰላም ይሉአችኋል።

፲፯ወንድሞቻችን ሆይ፥ እናንተ የተማራችሁ
ትን ትምህርት የሚቃወሙትን፥ መለያየትንና
ማሰናከያን የሚያደርጉትን እንድታውቁባቸው
እማልዳችኋለሁ፤ ከእነርሱም ተለዩ፤ ፲፰እነርሱ
ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያይደለ ለሆዳቸው
ይገዛሉና፤ በነገር ማታለልና በማለዛዘብም የብዙ
ዎች የዋሃንን ልብ ያስታሉ፤ ፲፱መታዘዛችሁም
በሁሉ ዘንድ ተሰምቶአል፤ እኔም በእናንተ ደስ
ይለኛል፤ ለመልካም ነገር ጠቢባን፥ ለክፉ ነገ
ርም የዋሃን እንድትሆኑ እፈልጋለሁ። ፳የሰላም
አምላክም ፈጥኖ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች
ይቀጥቅጠው፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ
ከእናንተ ጋር ይሁን፤ አሜን።

፳፩ከእኔ ጋር በሥራ የሚተባበረው ጢሞቴ
ዎስም፥ ከዘመዶቼ ወገን የሚሆኑ ሉቅዮስም፥
ኢያሶንም፥ ሱሲጴጥሮስም ሰላም ይሉአችኋል።
፳፪ይህችን መልእክት የጻፍኋት እኔ ጤርጥዮስ
በጌታችን ስም ሰላም እላችኋለሁ። ፳፫እኔንና
አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ በእንግድነት የተቀ
በለ ጋይዮስም ሰላም ብሎአችኋል፤ የከተማው
መጋቢ አርስጦስና ወንድማችን ቁአስጥሮስም
ሰላም ብለዋችኋል። ፳፭ከዓለም አስቀድሞ ምሥ
ጢሩ ተሰውሮ ስለ ነበረ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ
በማስተምራት ትምህርት ላይ ሊያጸናችሁ የሚ
ችለው እርሱ እግዚአብሔር ነው።

፳፮ይህም በነቢያት ቃልና የዘለዓለም ገዥ
በሚሆን በእግዚአብሔር ትእዛዝ በዚህ ወራት
ተገለጠ፤ አሕዛብ ሁሉ ይህን ሰምተውና ዐው
ቀው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ
ያምኑ ዘንድ። ፳፯ብቻውን ጠቢብ ለሆነው ለእ
ግዚአብሔር ክብር ይሁን፤ አሜን። ፳፬የጌታ
ችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር
ይሁን፤ አሜን።

በቆሮንቶስ ተጽፋ ለክንክራኦስ ማኅበረ ክር
ስቲያን በምትላላከው በፌቤን እጅ ወደ ሮሜ
ሰዎች የተላከችው መልእክት ተፈጸመች።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ለዘለዓለሙ
አሜን።

---

፲፮፥፲፫ ማር. ፲፭፥፳፩። ፲፮፥፳፩ ሐ.ሥ. ፲፮፥፩። ፲፮፥፳፫ ሐ.ሥ. ፲፱፥፳፱፤ ፩ቆሮ. ፩፥፲፬፤ ፪ጢሞ. ፬፥፳።